# የያዕቆብ መልእክት ጥናት

(አስተባባሪዎችና ለአስጠኚዎች)

(የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክ)
ዳላስ
ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

Ethiopian Evangelical Baptist Church
2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041
**www.eebc-dallas.org**
**Tel.2147030100**
**Fax 2147030161**

December 2011

***መግቢያ***

የመጽሐፉ ጅማሬ እንደሚያመለክተው የያዕቆብ መልዕክት በጌታ በኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ የተጻፈ መልዕክት ነው (ያዕ 1፡1፤ ማቴ 13፡55፤ ማር 6፡3)። ቅዱስ ያዕቆብ፣ በ62 ዓ.ም. ስለ ጌታ  በድንጋይ ተወግሮ ከመሞቱ በፊት፣ በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ መሪ የነበረ (ሐዋ 15፡13፣ 19-21፣ ገላ 2፡ 6፣9፣12) የጌታ ባሪያ ነው። መልዕክቱ እንደሚመሰክረው ያዕቆብ ይህንን መልዕክት የጻፈው ከአገራቸው ተለይተው በስደት ለነበሩ አይሁዳዊያን ክርስቲያኖት ቢሆንም፣ በውስጡ ያለው እውነት ግን በዬትኛውም ዘመን የሚኖሩትን አማኞች የሚመለከት ነው።

ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ለነበረችው ቤተክርስቲያን ከጅማሬዋ አንስቶ (40 ዓ.ም) እስከ በ62 ዓ.ም. እስከሞተበት ባሉት 22 አመታት ውስጥ መልክቱን መጻፉ ግልጽ ቢሆንም፣ በቤተክርስቲያን ታሪክ ግን፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት መጽሐፍቶች በቀዳሚነት የተጻፈ ነው ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ብዙዎች፣ ወንጌላት እና ሌሎች መልዕክቶች ከመጻፋቸው በፊት በ48 ወይንም በ 49 ዓ.ም. ሳይጻፍ እንደማይቀር ይገመታል።

ያዕቆብ  ይህንን መልዕክት በመጻፍ አማኞችን ሊያሳስብ የሚፈልገው አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ያላቸውን እምነት በሥራ ማሳየት እንዳለባቸው ለማስታወቅ ነው። በርግጥም ሰው የሚድነው በሥራ ባይሆንም፣ እውነተኛ እምነት ግን በሥራ ይታያል። በመሰረቱ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳስተማረው፣ አማኝ በእምነት የሚድንበት አንደኛው ምክንያት “መልካሙን ሥራ” ለማድረግ ነው (ኤፌ 2፡8-10)። ሆኖም ግን ሰው በክርስቶስ አምናለሁ ካለ የማመኑ አይነተኛ ምልክት በእምነቱ ምክንያት የሚያፈራው መልካሙ ሥራው ነው። ይህንን እውነት ለማስጨበጥ ያዕቆብ የተለያዩ የሕይወት ገጽታዎችን እያነሳ፣ በእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ ውስጥ አማኝ እንደ ክርስቲያን እንዴት መኖር እንዳለበት ያሳስባል።

ይህ የያዕቆብ መልዕክት ጥናት ሲዘጋጅ የቤተክርስቲያንም አይነተኛ አላማ አካሄዳችን በክርስቶስ ያለንን እምነት ማሳየት እንዳለበት ለማሳሰብ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው እና ታላቁ ሃላፊነት በክርስቶስ ኢየሱስ ማመን ነው። ከእምነት ወዲያ ግን አስተሳሰባችን፣ ንግግራችን፣ አድራጎታችን እና አካሄዳችን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን እምነት እንዲያንጸባርቅ ይገባል። በመሆኑም ይህንን ጥናት በምናጠናበት ጊዜ ሁሉ በክርስቶስ እናምናለን ካልን እምነታችንን በሥራ መግለጥ እንዳለብን እያሰብን እንድናጠና፣ ቤተክርስቲያን እና የዚህ ጥናት አዘጋጆች አደራ ይላሉ።

ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት አንድ**
**የእምነት መፈተን - ክፍል አንድ**
**የምንባብ ክፍል፡- ያዕቆብ 1፡1-12**

**የጥናቱ ዓላማ፡** *የእምነት መፈተን ፍጹማንና ሙሉዓን የሚያደርግ እንጂ የሚያጠፋን አለመሆኑን ማስገንዘብ።*

***መግቢያ***

*የመልዕክቱ ተቀባዮች የተበተኑ የእስራኤል ቤተሰቦች ናቸው። ከዚህ የምንረዳው ከተደላደሉበት ሁኔታ የወጡና በፈተና ያሉ ናቸው። ያዕቆብ ፈተናን አስመልክቶ ስለሚደርሱ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ መንፈሳዊ እውነቶችን ይሰጣል።*

*ያዕቆብ በዚህ ምዕራፍ እምነታችን ሲፈተን ከፉ ነገር እንደ ደረሰብን ብቻ አድርገን መቁጠር እንደሌለብን ያስገነዝበናል። እምነት የሚፈተን ነው። አንድ አማኝ በእምነቱ ሲፈተን የትዕግሥት ፍሬን ያፈራበታል እንጂ የሚጠፋበት አይደለም። ስለዚህ በእምነት ጉዞአችን ፈተና ሲገጥመን ወደ ከፍታ እየወጣን መሆኑን እንጂ ጉድ እንደመጣብን አንቁጠር።*

*በአለም ያልተለመደ አንድ እውነት በፈተና ደስ መሰኘት ነው። ለአማኝ ፈተና ለየት ያለ ግብ እንዳለው ክፍሉ በደንብ ያስረዳል። በዚህ ምዕራፍ በፈተና ስናልፍ እንደሙሉ ደስታ ልንቆጥረው የሚገባው ፍጹምና ሙሉዎች ስለሚያደርገን ነው። ፈተና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ህይወት በእኛ መኖሩ የሚታይበት አንድ መንገድ ነው።*

***አማኝና ፈተና* 1፡1-12**

*በዚህ ክፍል አማኝ በፈተና ሲያልፍ ልብ ሊላቸው ስለሚገቡ ሦስት ነጥቦች እንመለከታለን። በመጀመሪያ ፈተና ሁሉ አበሳን ልናይበት ብቻ አይመጣም፣ ስለዚህ መልካም ፍሬ ስላለው በትዕግሥት እንጽና። ሁለተኛ ስንፈተን ምን ማድረግ እንዳለብን ለማወቅ ጥበብን እንጠይቅ። ሦስተኛ በፈተናችን ወቅት የሚያስፈልገንን እንዲሰጠን የእምነት ጸሎትን እንጸልይ። ያዕቆብ እነዚህን ነጥቦች እንዴት እንደገለጣቸው እስቲ እንመልከት።*

1. *ፈተናን ሁሉ በትዕግስት ማለፍ* (1፡1-4 )

**"ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ"**፡- *ይህ ሀረግ ፈተናን በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዳናየው የሚያደርግ አባባል ነው። ፈተናዎቻችን ከእምነት የተነሳ የሚከሰቱ ስደቶች፤ በጽድቅ ለመኖር ካለን መሻት የተነሳ የሚፈጠሩ ትግሎች፤ ደዌዎች፤ የተፈጥሮ አደጋዎች እና ማንኛቸውም ከጌታ ፍቃድ ውጭ እንድናስብና እንድንመላለስ የሚያደርጉን ነገሮች ናቸው።*

***ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም፡-*** *የትዕግሥት ሥራው አንዳች ሳይጎድለን ፍጹማንና ሙሉዓን ማድረግ ነው። ይህ ዕድገትን የሚያመለክት አባባል ነው። ብስለት እንደሚታይበት ሰው ነገራችን የምናይበትና የምናደርግበት መንገድ ነው። ደግሞም በነገሮች የማንፍገመገም፣ ነገር ግን የምንጸና መሆናችንን የምናሳይበት ጉልበት ነው።*

*ከቁጥር 1-4 ባለው ክፍል በፈተና ሆኖ ደስታን ለመለማመድ፤ ልንታገስ ይገባል። ያዕቆብ የሚናገረውን መልካም ፍሬን ለማግኘት በማንኛውም ፈተና ውስጥ ስንሆን ራሳችንን ለጌታ በመስጠት መታገስ ተገቢ መሆኑን ነው።*

2. *በፈተና የሚያልፍ ጥበብን ይለምን* (ቁጥር 5)

*በፈተና ውስጥ ስንሆን የሚያሻን ነገር ጥበብ ነው። ጥበብ የፈተናውን አይነት፣ ምንጩን ዓላማውን እንድንገነዘብ ይረዳናል። ስለዚህ ጥበብ በዕለት ኑሮአችን፣ በፈተና ወቅት እንዴት ከኃጢአት እንደምንርቅና ጌታን ከማያስከብሩ ግኑኝነቶች እንደምንለይ የሚያስገነዝበን ነው። በፈተናችን ወቅት ጥበብ የጎደለን ሆነን መገኘት ለሽንፈት ይዳርገናል።*

*ጥበብን ስንሻ በልግስና ሰጪ እንዳለ በማመን ያለጥርጥር ልንጠይቅ ይገባል። እየዋለሉ መጸለይ ግልጽ የሆነ ምላሽን አያስገኝም። በሁለት እሳብ እያነከሱ የሚቀርብ ጸሎት መልስ የለውም። ጥበብን ለማግኘት በእምነት እንጂ በጥርጥር የሚጠይቀው አንዳች አያገኝም።*

*የሚለመነው ጌታ በልግስና እና ማንንም ሳይነቅፍ የሚሰጥ መሆኑን ያዕቆብ ያሳስባል። ለመስጠቱ ጥያቄ የለውም፤ ስለሚመልስበት ሁኔታዎች ደግሞ ምንም መስፈርት የለውም። ጥበብን ከሚሻ የሚጠበቅበት አንዳች የለም፤ ያለጥርጥር ከመጠየቅ በቀር።*

3. *ሁሉ ስለሚያልፍ ጽና* (ቁጥር 9-11)

*ያዕቆብ የፍጥረትን ሁኔታ በማንሳት ነገሮች ሁኔታዎች እንደሚያልፉ ይናገራል። መደህየት ሆነ መበልጸግ ሁለቱም እንደ ሣር ያልፋሉ። ከአበሳውና ከኑሮው ሁኔታ የተነሳ ፍጻሜው የተቃረበ የሚመስለው ደሃ ብቻ ሳይሆን ባለ ጠጋም ዝለት እንደሚገጥመው ይናገራል። የተሳካለት የሚመስለውን አይተህ አበሳህን ትልቅ አታድርገው ሁሉ ያልፋል።*

*ሰው ሁሉ ትክክለኛ የሆነ አመለካከትን በመያዝ ሕይወትን መምራት አለበት። ሁሉ ስለምያልፍ የተዋረደ የውርደት ዘመኑ እንደሚያበቃ፤ የከበረው ደግሞ ነገሮች እንደማይጸኑ በማስብ መኖር ጥበብ ነው።*

4. *በፈተና የሚጸና የተባርከ ነው* (ቁጥር 12)

*በፈተና መጽናት ብድራት ያለው ነገር መሆኑን በግልጽ ከዚህ ቁጥር እንረዳለን። የሚፈተን የተባረከ ነው። የዕድገት ጉዳይ ብቻ አይደለም። በእምነቱ ሰው ሲፈተን በምድር ነገሮችን በድል አልፎ ማየት ብቻ ሳይሆን ከዛ የበለጠ ነገር የሚያገኝ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። አማኝ በእምነቱ ጸንቶ ጌታውን ካከበረ የሕይወት አክሊልን ይቀበላል። ስለዚህ አሁን በምድር ያለው ፈተና ለነገው ለዘላለማዊው ዓለም ብድራትን የማካበቻ መንገድ ነው።*

**መደምደምያ፡** *ፈተናን በትዕግሥት ማለፍ፤ ጌታን እንድንበድል ከሚገፋፉን ፈተናዎች ደግሞ መራቅ በሰማይና በምድር በረከት አለው። ጌታን በማመን መከራን መቀበል የብድራት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የጌታን ህልውና በህይወታችን ምዕራፎች ሁሉ በአስደናቂ ሁኔታ ማየት ነው።*
*የፈተናችንን አይነት መለየት ጥበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል በግፍ ሥራችን ምክንያት መከራን የምንቀበል ሳይሆን መልካምን እየሠራን ለምናልፍበት መከራ ጌታ ብድራትን ለኛ መለየቱን አንዘንጋ።* (1ጴጥ. 2፡19-20፤ 5፡ 9-10)

***የመወያያ ጥያቄዎች***

***ማሳሰቢያ ለሁሉም የመወያያ ጥያቄዎች፡-*** *መጻፍ የሚችሉ መልሱን ጻፉ፣ተወያዩም።*

1. በቁጥር አንድ ላይ ጸኃፊው ራሱን እንዴት ነው የገለጸው? ተቀባዮቹንስ?
2. ከቁጥር 2-4 ጸኃፊው ወንድሞቹ የሚላቸው የሚያልፉበትን ፈተና እንዴት ነው እንዲመለከቱት የሚያበረታታቸው? ለምን? በቁጥር 5 ላይ ስለፈተናዎች መወገድ ሳይሆን ስለጥበብ ማንሳቱ ምን ያመለክታል? ስለሰጪውና ስለ ጠያቂዎች ምንድነው የተገለጠው?
3. በቁጥር 6-8 ጥበብ የሚጎድለው እንዴት እንዲለምን ነው የተመከረው? ይህ “ለሁሉ” ከሚለው የቁጥር 5 አሳብ ጋር እንዴት ይዛመዳል? የፀሎቱን መልስ በተመለከተ ክፍሉ ምን ያሳየናል?
4. በቁጥር 9-11 ተፈጥሮንና የሰው ልጆችን ሁኔታ እያነጻፀረ የሚዘረዝረቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ከእምነታቸው መፈተን ጋር ምን ያገናኘዋል?
5. በቁጥር 12 በፈተና ስለሚያልፍ ሰው ምን ምን ይናገራል? ስለ በረከትና ተስፋስ?
6. በ“ልዩ ልዩ ፈተና” ስለመጽናት ያለህ ልምምድና መረዳት ምን ነበር? አሁንስ? ያለፍክባቸውስ ፈተናዎች አሉ? አንድ ሰው ይመስክር።

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ሁለት**
**የእምነት መፈተን - ክፍል ሁለት**
**የንባብ ክፍል፡ 1፡12-18**
**የጥናቱ ዓላማ፡** በፈተና ወቅት ስለፈተናችን ምንነትና ስለፈተኙ በቂ ግንዛቤን ይዘን መጽናት እንዳለብን ማስገንዘብ።

*መግቢያ፡-*
*ፈተናን ዝም ብለን መጋፈጥ የለብንም። አንዳንድ መሰረታዊ ነገሮችን ልብ ብለን ማጤን ተገቢ ነው። ፈተናው ምንድን ነው? ፈተናዬ ከምን የተነሳ ነው? የፈተናዬ ምክንያቱ እኔው ነኝ ወይ? እነዚህን ለመሳሰሉ ጥያቄዎችን የምንሰጠው ምላሽ በጥበብ ነገሮችን እንድናይና ያለማጉረምረም እንድንጸና ጉልበት ይሆነናል።*
*በመጀመሪያው ክፍል ስለ ፈተና ፍሬ፣ ስለ ጥበብ አስፈላጊነት እና ስለ ፈተናችን ጊዜያዊነት በቂ ትምህርትን ሰጥቶናል። በሚቀጥለው ክፍል ያዕቆብ ስለፈተና እና ስለፈታኙ በማወቅ ፈተናን እናልፈው ዘንድ ይመክረናል።*

***ፈተናን፣ ፈታኙንና መፍትሄውን መለየት 1፡13-18***

**1. የእምነት መፈተንና እግዚአብሔር** 1፡13
*ብዙዎቻችን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስንገባ "ጌታ ሆይ ለምን ትፈትነኛለህ?" እንል ይሆናል። ይህን አስመልክቶ፣ ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ሁለት ነገሮችን ይነግረናል። አንደኛ እግዚአብሔር በክፉ (ለመጣል) አይፈትንም። ሁለተኛ እግዚአብሔር ራሱ በክፉ አይፈተንም። ከነዚህ አባባሎች በአጭሩ የሚለን ነገር ቢኖር አምላካችን ይህን እንደማያደርግና ከዚህ ነጻ የሆነ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ለማጠንከር እንጂ ማንንም እንደ ሰይጣን በኃጢአት ለመጣል አይፈትንም።*
*እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅ ስለሆነ የክፋት ሥራ በእርሱ ዘንድ የለም። ከማንነቱ (ከባህርይው) ጋር የሚጻረር ነገርን ማድረግ አይችልም። ስለዚህ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ የሚል አባባል ተገቢ አይደለም። ማስተዋል፣ ጥበብ የጎደለው አባባል ስለሆነ መታረም አለበት። ታዲያ ፈተና ከየት ይመጣል?*

**2. ምኞትና የሰው ልጅ ፈተና** 1፡14-15
*በያዕቆብ መልዕክት የፈተና ምንጩ ከውጭ የሆነ ሳይሆን የሰው ልጅ የውስጥ ጉዳይ መሆኑን ያሳያል። ሰው በራሱ <u>ምኞት</u> ወደፈተና ሊገባ ይችላል። እንዴት ለሚል ምላሽ፣ ጸሓፊው በምኞት በመሳብና በመታለል ፈተና እንደሚመጣ ይናገራል። ሰው በምኞቱ ለተለያዩ ነገሮች (ለትዕቢት፣ ለብልጥግና ወዘተ) ሲሳብና ሲታለል ለፈተና አልፎ ይሰጣል። በፈተናም ይወድቃል። እግዚአብሔር እኛን አይፈትነንም፣ የራሳችን ምኞት ግን ለፈተናዎች ያጋልጠናል።*
*ምኞት የሰው ልጅን የምትነዳው ደረጃ በደረጃ ነው። በቃሉ እንደተጠቀሰው "ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች። ኃጢአት ከአደገች በኃላ ሞትን ትወልዳለች።" ይህ አባባል ምኞት በጊዜ ካልታገደች ወይም የቀና መንገድ ውስጥ እንድትገባ ካልተደረገች ፍሬዋ ከባድ እንደሆነ ነው።*
*ስለዚህ በፈተና ውስጥ ስንሆን በመጀመሪያ ማየት ያለብን የውጭ ኃይልን ሳይሆን ራሳችንን መሆኑን ልብ እንበል። እኛን የሚፈትነን አሮጌው ሥጋችን እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። በምንም መልኩ ጌታ መልካም ነገርን አድራጊ እንጂ ፈታኝ አይደለም።*

**3. እግዚአብሔር ፈታኝ ወይስ የበጎ ሥጦታ ባለቤት** 1፡16-18
*መሳሳት የሌለብን ነገር "ጌታ የበጎ ሥጦታና የፍጹም በረከት ባለቤት" መሆኑን ነው። እግዚአብሔር መልካም እንጂ ፈታኝ አይደለም። እግዚአብሔርን እንደፈታኝ አድርጎ ማስብና መቁጠር ጌታን አለማወቅ ነው። ጌታ እግዚአብሔር በባህርይው መልካም ነው። ስለዚህ እርሱ ሌላ ሊሆን አይችልም "የበጎ ሥጦታና የፍጹም በረከት ባለቤት" ከመሆን በቀር።*
*አትሳቱ በእግዚአብሔር ዘንድ መለዋወጥ የለም። አንዴ መልካም ሌላ ጊዜ ፈታኝ የመሆን ባህሪይ የለውም። እርሱ ፍጹም መልካም ነው። ስለዚህ ሰው ሊስት (ሊታለል) አይገባም ማለትም እግዚአብሔር እንደፈተነው በማሰብ ጥያቄን በመጠየቅ ራሱን ማታለል የለበትም(1ቆሮ 6፡9፤ 15፡33፤ ገላ 6፡7፤ 1ዮሐ 3፡7)*
*እምነታችንን በጌታ እንደተፈተነ አድርጎ መቁጠር፤ እርሱ ሲፈጥረን እና በልጁ ደም ሲዋጀን ካለው ዓላማ ጋር የሚሄድ አይደለም። እርሱ "ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል እስቦ . . ." በጎን በኛ ያደርግ ዘንድ ነው የወለደን። [ዘፀ. 34፡22፣ ዘሌ. 23፡10] መቼም ጌታ ለሚታመኑት ያለው ሀሳብ የሰላም አሳብ ብቻ ነው። በጎነት ነው!*
*ስለዚህ እምነታችን ሲፈተን ጌታ እንደ ፈተንን ሳይሆን ማሰብ ያለብን ማንነቱን በጥበብ መረዳት አለብን። እንኳን ሊፈትነኝና መታሰቢያየን ሊያጠፋ እርሱ በእኔ ላይ ያለው አሳብ በጎ ነው ብለን ነው መጽናት ያለብን።*
*ይህ መረዳት ትዕግስት ምንም ሳይጎድለን የታቀደልንን ግብ እንድንደርስ ሥራዋን በኛ እንድትጨርስ ያደርገናል።*

***መደምደምያ፡*** እግዚአብሔር በጎነትን እንጂ ክፋትን ማድረግ ባህርይው ስላልሆነ ስንፈተን በእርሱ ላይ ከማጉረምረም ይልቅ ጥበብን እንጠይቀው። ይህም የፈተናችንን ምንጩንና መፍትሔውን እንዲያሳየን ይረዳናል። በኛ ላይ ያለው አላማ በጎ መሆኑን ተረድተን እንድንጸና ሁለንተናችንን ወደ እርሱ እናቅና።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁጥር 13 የፈተናን ምንጭ በተመለከተ ምንድን ነው የተገለጸው? በፈተና የሚያልፍስ ሊገነዘበው የሚገባ እውነት ምንድን ነው? ተውያዩ

2. በቁጥር 14 ላይ የተገለጠ የፈተና ምንጭ ምንድን ነው? በምኞት ሲሳብና ሲታለል የሚሉት ቃላቶች በፈተና ውስጥ ሰው ራሱን ስለማግኘቱ ምን ያመለክታሉ? በቁጥር 15 ምኞት፣ ኃጢአት እና ሞት የተገለጠው እንዴት ነው? እንዴትስ ትረዳዋለህ? (ቁጥር 16-17)አትሳቱ የሚላቸው ስለምን ጉዳይ ነው? ስለ መልካም ነገር ምንጭና ማንነቱ የተገለጠውን ተወያዩበት።

3. የጌታ በጎነትና ማንነት በእምነታቸው ለሚፈተኑት ምን ተስፋ ይሰጣቸዋል?

4. ቁጥር 18 ላይ ያለው አሳብ ስለ አማኞቹ ምን ይናገራል? ይህን መገንዘብ እንዴት ነው በፈተናችን እንድንጸና የሚያግዘን?

5. ቁ.18 "የብኩራት ዓይነት እንድንሆን" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ አባባል አማኝ በእምነቱ ሲፈተን ሊኖረው ስለሚገባው ግንዛቤ ምን ያስተምርሃል?

***የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ሦስት***

***የእምነት መፈተን - ክፍል ሦስት***
**የንባብ ክፍል፡- 1፡19-27**
**የጥናቱ ዓላማ፡-** አንደበታችንን በመግዛትና ከቃሉ የተማርነውን በትክክል በመተግበር መኀልበት እንዳለብን ማስገንዘብ።

*መግቢያ፡*
*ያዕቆብ በዚህ ክፍል ስለ አንደበትና በተማሩት ቃል ስለመኖር ታላቅ ምክርን ይሰጣል። በፈተና ወቅት በድል እንድንወጣ አንደበታችን መጠበቅና እንደቃሉ መመላለስ ተገቢ ነገር ነው። ቀደም ባሉት ቁጥሮች እምነት ሲፈተን ጸንተን እንድንቆም ጥቂት ምክሮችን ሰጥቶን ነበር። እስከ አሁን ባየናቸው ጥናቶች ስለፈተና ግብ፣ ስለ ጥበብ አስፈላጊነት፣ ስለ ፈተናዎቻችን ጊዜያዊነት፣ ስለፈተናዎቻችን ምንጭ እና ስለጌታ መልካምነት ተመልክተናል።*
*አንደበታችንን ካለመጠበቅ ከሚመጣ ፈተና እና ቃሉን ካለመጠበቅ ከሚገኝ ፈተና መጠበቅ እራሱን የቻለ በረከት ነው። በዚህ ክፍል ደግሞ አንደበታችንን መጠበቅና እንደቃሉ መራመድ ለግል ህይወታችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ከውጣውረድና ከፈተና ምን ያህል እንደሚጠብቁ እንመለከታለን።*

***ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ*** 1፡19-21፣ 26

- *የምትፈጥንበትንና የምትዘገይበትን ለይ፡- (1፡19-20፣26)*

*ያዕቆብ ስለአንደበት በምዕራፍ 3 በስፋት ይናገራል። በዚህ ክፍል፣ በቁጥር 19 ና 26 ለመናገር የዘገየ ስለመሆን ይናገራል። በማስተዋል የምናደምጥና ለመናገር የተቆጠብን መሆን ተገቢ ነው። በብዙ ንግግር ውስጥ መሳት ያለ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ብዙ የሚናገር ሰው ለማዳመጥ ጊዜ የለውም። ያዳመጠ ቢመስልም እንኳን በሥርዓት ላላዳመጠው ሀሳብ ምላሽን ለመስጠት ነው የሚያሰላስለው።*
*ቁጥር 18 ላይ በቃሉ እንደወለደን ይናገራል። ይህ ቃል መውለድ ብቻ ሳይሆን ለህይወታችን የጥበብ ምንጭ ነው። ስለዚህ አድማጭ አለመሆን፣ ሊደመጥ የሚገባውንና ፈውስ የሚሆነንን የጌታ መንፈስን ባለማዳመጥ ጉዳት ላይ ይጥላል።*
*ያልተገራ አንደበት ብዙ ጣጣን ያመጣል። ገደብ የሌለው ንግግር ክርክርን ያስነሳል አልፎም አለመግባባትንና ቁጣን ያስከትላል፤ ይህ ደግሞ መወገድ አለበት። ያዕቆብ ለዚህ ምክንያትን ሲሰጥ "የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ" መሥራት እንደማይችል ይናገራል።*
*ስለዚህ ለመስማት የፈጠንን ለመናገር ግን የዘገየን መሆን ለሰው ልጅ እረፍትና ለጌታ ክብርን ያመጣል። ብዙ ያልተናገረ ብዙ ስህተት ውስጥ አይገባም።*

- የሚወገድና የሚያዘውን ለይ፡- (1፡21)

የክፋትን ትርፍ አስወግድ ቃሉን ግን አጥብቀህ ያዝ። በውስጣችን የተቀመጠውን የጌታ ቃል በሙሉ ጉልበቱ በእኛ እንዳይሠራ እንቅፋት የሚሆነውን ሁሉ ማስወገድ አለብን። ያዕቆብ ለሚጽፍላቸው አማኞች እንዲህ ይላቸዋል "የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፣ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።" ይህ አባባል የዳኑበትና በውስጣቸው ያለውን የጌታን ቃል የሚያመለክት ነው።

- ከምኞታችን የሚወጣው ሁሉ የተባረከ አሳብ አይደለም። ስለዚህ የክፋትን ትርፍ እንቢ ማለትና የቃሉን ምሪት በየዋህነት መቀበል ይገባል። ቃሉን መቀበል ደግሞ በተግባር መተርጎም ነው።
- የተማርነውን እንተግብር 1፡22-27

ቃሉን መስማት መልካም ነው። የሰሙትን መተግበር ደግሞ ይጠበቃል። ያመኑትን በሥራ መተርጎም የያዕቆብ መልዕክት ማዕከላዊ ትምህርት ነው። እውነተኛ አማኝ የሰማውን በህይወቱ ይለማመደዋል።

- ራሳችሁን አታስቱ፦ (1:22-25)

የሰሙትን አመለተግበር ልክ ፊቱን በመስታወት አይቶ እንደሚረሳ ነው ይላል። ሰው መስተዋት ከተጠቀመ በኃላ በፊቱ ላይ ያለውንና መወገድ የሚገባውን ለማስወገድ እርምጃን እንደሚወስድ፤ ቃሉን የሰማ የሰማውን ቸል ሊል አይገባም። ጸኃፊው የተጠቀመበት ምሳሌ የሚያመለክተው ሰሚው የመረዳት ችግር እንደሌለበት ነው። በመስታወት አይቶ ጉድለትን የማያይ የዓይን ችግር ያለበት ብቻ ነው። ችግር ካለበት ደግሞ መስተዋትን አይጠቀምም።

በዚህ ክፍል "ፍጹሙን ህግ" የሚለውን ቃል ከሙሴ ህግ ጋር የግድ መያያዝ የለበትም። በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ቃል ማለቱ ነው። ይህን ፍጹም የሆነውን ህግ ሰማ የሚባለው ሰው የመረዳት ችግር ያለው አይደለም። ስለዚህ "ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ" ሲል እንደው ላይ ላዩን የሆነ ነገር አይደለም። አልገባኝም ለሚል አሳብ ዕድልን አይሰጥም። ጠንከር ያለ ነገርን ነው የሚያሳየው።

የሰሙትን ቃል በህይወት መለማመድ በረከትን ሲያስከትል፤ ተገቢውን ምላሽ አለመስጠት ደግሞ ጉድለትን ያስከትላል። ስሙን ብንጠራም፤ የምናመልከው መሆናችን ቢነገርም ተግባራችንን ከነዚህ ሁሉ የበለጠ ነው። (መዝ. 1)

**እውነተኛ አምልኮ፦ 1: 26፣27**

እውነተኛ አምልኮ የሚገለጥባቸው ሁለት የሚያያዙ አሳቦችን በምዕራፉ መጨርሻ ይሰጣል። የመጀመሪያው አንደበትን (ንጽህና) መግታት ሲሆን ሁለተኛ ደካሞችን መርዳት ነው።

የእውነተኛ አምልኮ ትርጉም ሥርዓትን ከመፈጸም ያለፈ ነው። ቃሉን መስማት ለብቻው በተግባር ካልተገለጠ ከንቱ ነው። አንደበትን እንደፈለገው እየተጠቀመበት ራሱን እንደ እውነተኛ አምላኪ መቁጠር መሳት ነው።

ንጹህ የሆነው አምልኮ ግን በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ያለው፤ የቃላት ብዛት ያለበት ሳይሆን የልብ የሆነ የተቀደሰ ምግባር ያለበት ነው። በችግር ያሉትን ማሰብና እነርሱን መርዳት። ከቃሉ የሚማረውን ያለምንም መቆጠብ በተግባር የሚያውል እምነቱን በሥራ የሚገልጥ ነው። ይህ ሰው በሥራ ለመዳን የሰማውን በተግባር የሚያውል ሰው አይደለም። ይህ ሰው በልቡ ለተተከለው የጌታ ቃል ያስገዛ እንደመልካም መሬት ራሱን ለቃሉ የሰጠ፣ ያስገዛ ነው።

***መደምደምያ፦*** ክርስትና ከቃል ያለፈ ያመኑትን በተግባር የሚተርጉሙበት መንፈሳዊ ጉዞ ነው። ይህ ህይወት ፈተና አለበት። ለያዕቆብ በእምነቱ የሚፈተን አማኝ ፈተናውን፣ ምንጩን እና ግቡን በሚገባ የተረዳ ሰው ነው። የያዕቆብ መልዕክት አማኝን ለራሱ ብቻ የሚኖር እንደሆነ ሳይሆን አምላኩን ለማክበርና ሌሎችን ለመጥቀም ሚዛናዊ በሆነ የህይወት ዘይቤ የሚመራ መሆኑን ነው የሚያስተምረን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ***ያዕቆብ በቁጥር*** 19 ላይ የፈጠነና የዘገየ ሁን እያለ የሚናገረው በምንና ስለምንድን ነው? ለምን? [ተጨማሪ ጥቅስ ምሳሌ 10፡19-21]
2. የእግዚአብሔርን ጽድቅ የማይፈጽመው ምንድን ነው? ለምን? [ተጨማሪ ምሳሌ 14፡19፤ 15፡1]
3. በቁጥር 21 አስወግዱና ተቀበሉ የሚላቸው ነገሮች ምንድ ናቸው? ይህን የሚለው ከምን ጋር በማያያዝ ነው? እንዴት ነው በፈተና ለመጽናት የሚረዳን?
4. በቁጥር 22ና 23 ልንስተው ስለማይገባን ነገር የሚመክረን ምክር ምንድን ነው? የሚሰጠን ምሳሌ ምንድን ነው?
5. 1:23 እንዴት ነው ፊትን በመስታዋት ማየት የሰሙትን በተግባር መለማመድን የሚገልጸው?
6. 1:25"ፍጹሙ ሕግ" ተብሎ የተጠቀሰው የትኛው ነው? ይህ ሕግ ምን ያስገኛል? በዚህ መጽናት ማለትን እንዴት ትረዳዋለህ?
7. እግዚአብሔርን ያመለከ አይምሰለው የተባለው ምን አይነት ሰው ነው? የዚህ ሰው አምልኮ ምንድን ነው?1:26
8. ንጽህ አምልኮ ምንድን ነው? እንዴት ነው የሚገለጸው? [ማቴ. 25፡36፣43]
9. "በዓለም ከሚገኝ እድፍ" ሰውነትን መጠበቅ ማለት ምን ማለት ነው? መዝ 1 ገላ 5፡6 1ጴጥ 2፤11-12
10. ከያዕቆብ መልዕክት ያለህን የእምነት ጉዞ በተመለከተ የተማርከውን ለቡድንህ አካፍል። ለምን አይነት እርምጃ ነው የተነሳሳህው?

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት አራት**
**በክርስቶስ እምነት ላለው ሰው አድልዎ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አይደለም።**
**ያዕ 2፡1-13 (ክፍል አንድ)**
**የጥናቱ ዓላማ፡** በጌታ ትምህርት አድልዎ እንደሌለ ማሳወቅና እንደ እግዚአብሔር ልጆች በቤተክርስቲያንና ከቤተክርስቲያንም ውጪ ለሰዎች ያለን ቦታ ክርስቲያናዊ ፍትህና እኩልነትን የሚያንጸባርቅ መሆን እንዳለበት ማሳሰብ።

*መግቢያ*
ያዕቆብ በመልዕክቱ እምነታችንን ማሳደግና ማጥራት የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎችን ይናገራል። እንደተማርነው ምዕራፍ አንድ ላይ የመልዕክቱ ተቀባዮች ሌላ ዓይነት ፈተና ቢገጥማቸውም፤ ምዕራፍ ሁለት ላይ ደግሞ አድልዎ (የሥነ ምግባር ፈተና) በመካከላቸው ሰፍኗል። ይህ ደግሞ አይሁዳዊያንም ሆኑ ሌሎች በባህላቸውና በሃይማኖታቸው ከተለማመዱት ኑሮ ውጪ ነው። ነገር ግን አሁን የጀመሩት በክርስቶስ ያላቸው እምነት ሰዎችን የሚያየው እንደለመዱት ዓይነት ልምምድ አይደለም። ሁሉም በጌታ እኩል ነው።

1. **አድልዎ ለምን አይደረግም?** ይህ መልዕክት እንደሚያመለክተን በመልዕክቱ ተቀባዮች ጉባኤ መካከል አድልዎ እንዳለ ያመለክታል። ስለዝህ የጌታ ቃል አድልዎ አያስፈልግም ይላል። ግን ለምን? ያዕ 2፡1 እድልዎ መደረግ ከሌለባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ ብሎ ያስቀመጠው በክርስቶስ እምነት ያላቸው **ወንድሞችና እህቶች (አንድ ቤተሰብ)** ስለሆኑ ። ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን። ያዕቆብ በመልዕክቱ 15 ጊዜ ከተጠቀማቸው "ወንድሞች" ከሚል ቃል በያዕ 2፡1 የተጠቀሰው አንዱ ነው። ማንም ፍቅር ባለበት ቤተሰብ አድልዎ አያደርግም። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሁለተኛው ምክንያት **በከበረ ጌታ ስለምንጠየቅ ነው።** ይህ የከበረ ጌታ ደግሞ ሁሉን አዋቂ፣በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ፣ሁሉን ቻይ፣ዘላለማው እናም ሉዓላዊ ነው። እርሱ ደግሞ የሁሉም ፈራጅ ነው። ከእርሱ ምንም አይደበቅም። ብዙ የቃሉ አስተማሪዎች እንደሚስማሙ ያዕ 2፡1 አድልዎ እንዳያደርጉ የተነገራቸው በትዕዛዛዊ ዐ/ነገር እንደሆነ ነው። አድልዎ ቢያደርጉ ግን የከበረ ጌታ በማይፈልገው ከሥነ ምግባር ፍርድ ሥር ናቸው።
እምነትና አድልዎ አንድ ላይ ይዞ መቀጠል ትርፉ ሥጋን የጦር ሜዳ ማድረግ ብቻም ሳይሆን ጌታንም ማሳዘንና ለፍርድ መዘጋጀት ነው። አድልዎ የምናደርግ ከሆነ ሌላው የምገጥመን ችግር ደግሞ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ ክቡር እና በክርስቶስ ደም የተዋጀ ሆኖ ሳለ በምድራዊ ሚዛን መመዘናችን ይሆናል። በማንም ሰው ላይ ምንም ዓይነት ክፍፍልና አድልዎ ተጠያቂነትን ያስቀምጣል። ንስሃ ገብተን አዲስ ጉዞ እንጀምር።

**2. በያዕ 2፡2 ላይ አድልዎ አይደረገበት የተባለው "ድሃ" ማን ነው፡?** በርግጥ አድልዎ በማንም ላይ እንዲደረግ የእግዚአብሔር ቃል ባይፈቅድም በያዕ መልዕክት **ድሃ** የሚለው ቃል የሚያመለክተው በሥራ ፈትነት ድሃ የሆኑትን ሳይሆን ሥራ አጥተው ወይንም እየሰሩም በሮማዊያንና በግሪኮች በሌሎችም የመደብ ክፍፍልና የባሪያ አገዛዝ ምክንያት በኑሮ ችግር የተጎዱ ናቸው። ያዕ 2፡2-3 በዚህ ክፍል ያዕቆብ ምድራዊና ውጫዊ የውበትና የክብር መለኪያዎች የሆኑትን ውስን ምሳሌዎችን ያስቀምጣል። መልዕክቱ በተጻፈበት ወቅት ድሆች በብዙ ራሳቸውን ማስጌጥ ቀርቶ ከአንድና ከሁለት ልብስ በላይ ማግኘትም አስቸጋሪ ነበር። ከፍተኛ የኑሮ ችግርና ረሃብም ነበረባቸው። የያዕቆብ መልዕክት እነዚህን ይበል እንጂ ተመሳሳይ ውጫዊና ምድራዊ አታላይ ነገሮች ብዙ እንደሆኑ እናውቃለን (ለምሳሌ፡-ሥልጣን፣ትምህርት፣ዘር፣ዕድሜ፣ጾታ፣ሀገር ወዘተ)። በነዚህ መለኪያዎች ተመሥርተን ምንም ዓይነት አድልዎ እንድናደርግ የከበረ ጌታ አይፈቅድም። ጌታን የያዘ ሰው በእግዚአብሔርና በእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ዘንድ ድሃ አይደለም። ይልቁንም የእምነት ባለጠጋ ናቸው። ይህን እውነት በማቴ 5-7 የተጠቀሰው የተራራው ስብከት በተባለው በጌታችን ትምህርት በጥልቀት ያስተምረናል።

**3. አድልዎ ቢደርግስ (ምን መሆናችን ነው)?** ያዕ 2፡4 እንደሚነግረን የጌታን ልጆች የመለያየትና አድልዎ የማድረግ ክብደቱ በክፉ ሃሳብ መያዝ እንደሆነ ይነግረናል። ይህም ለፍርድ የእግዚአብሔርን ቦታ ለመያዝ መሞከራችንን እንደሆነያሳያል። በዮሐ ወንጌል 7፡24 ጌታ ኢየሱስ የሰውን ፊት አይተን መፍረድ ትተን ቅን ፍርድ እንድንፈርድ ያዘናል። እንዳይፈረድብን መፍረድ የለብንም።

**4. አድልዎ ማድረግ የሌለብን መቃወሚያ ሀሳቦች (ምክንያቶች) ያዕ 2፡5-13**
*ሀ.* ያዕ 2፡6 እንደሚናገረው በጊዜው የነበሩ ባለጠጎች የእግዚአብሔርን ቃል ያልተገነዘቡና የማይኖሩ፤ ለክርስቲያን ድሆች የነበራቸው እውቀታቸውና አመለካከታቸው እንዳልዳኑ ሰው ነበር(እነዚህ ባለጠጎች የዳኑም ያልዳኑም ሊሆኑይችላሉ)። ነገር ግን የጌታን ስም የሚያቃልሉ ወይንም የሚሳደቡ ናቸው ተብለዋል። በርግጥ ማወቅ የምገባን ነገር ቢኖር ሰው በንግግርም ይሁን በድርጊት እግዚአብሔርን ሊሳደብ ይችላል። በጊዜው በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረው ችግር በቤተክርስቲያንም ነበር። እግዚአብሔር በእምነት ያበለጸጋቸው፤ መለኮታዊ ጥበብ ያላቸው ነገር ግን በምድራዊ ነገር ድሃ የሚመስሉ ናቸው። ስለዚህ የእምነት ባለጠጎችን ከምድራዊ ነገር ባለጠጎች ጋር ማነጻጸር አያስፈልግም። ምድራዊ ብልጥግና መንፈሳዊ ብልጥግናን መከተል አለበት እንጂ መምራት የለበትም። ምድራዊ ነገር ጠፊና አላፊ ነው። ታዲያ ዬትኛው መስፍርት መዝኖብን እንደሆነ ራሳችንን መመርመር እንችላለን። ለማጠንከር ያህል በቤተክርስቲያን ከአማኞች ጋር ካለን

ግንኙነት ሌላ በተሰጠን የሥራ ቦታና ድርሻ ስለ እግዚአብሔር በማይውቁ ሰዎች መካካል እኩልነትን በኃይል ማብራት አለብን።

ለ. 2፡8 አድልዎ የፍቅርን ህግ የሚቃረን የሥጋ ሥራ ነው። በገላ 5፡19 ላይ ከተጠቀሱ የሥጋ ሥራዎች "የመለያየት" ኃጢአት በዚህ ቦታ ሥራውን ያከናውናል።"የንጉሥ ሕግ" (ያዕ 2፡8) ይህንን ህግ ያዕቆብ ከዘሌ 19፡18 ጋር ይዛምዳል። ይህ የንጉሥ ሕግ ደግሞ የጌታችንም ትምህርት መሆኑን በወንጌል ተጠቅሷል (በማቴ 22፡36-40፤ማር 12፡28-31)። ክርስቲያኖች አድልዎ የሚያደርጉ ከሆኑ ኃጢአት እያደረጉ ወይንም ይህን የፍቅር ህግ እየተላለፉ እንደሆኑ ያዕ2፡9 እንደሚከተለው ይናገራል " ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል"።
**5. በያዕ 2፡8-13 ኃጢአት ሁሉ እኩል ነው?** ኃጢአት ሁሉ አንድ ነው፤ማንም ላይ አድልዎ ማድረግ (መለያየትም) ኃጢአት ነው። በዚህ ክፍል መሠረት በጌታ ቤት የሚሰራ ኃጢአት ሁሉ እኩል ነው። ለዚህም ያዕቆብ ከብሉይ ኪዳን ህግ ለማብራሪያ እንዲሆን ያመጣል ማለትም ያመነዘረም የገደለም እኩል ነው ይላል። ውጫዊ ታይታ ከውስጣዊ ማንነት ጋር ካልታረቀ እራስን ለፍርድ ማቆየት ይሆናል።፡ስለዚህ አድልዎ ማድረግ ቢሆን ይቅርታ አለማድረግ ወይንም መስረቅም እኩል ኃጢአት ናቸው። አድልዎ ማድረግም ከሌላው ኃጢአት ጋር እኩል ኃጢአት ነው። በውጫዊ ማንነት ሰውን እንድንፈርድ ጌታ አይፈቅድም። እግዚአብሔር እንዴት እንደፈረደብን የምናውቅ ከሆነ በሌሎች ላይ ስንፈርድ ማለትም ድሃ ወይም ሃብታም ብለን ስንልና ቦታ ስንሰጥ መጠንቀቅ አለብን። ቃላችንና ልባችን አንድ መሆን አለበት። ስንናገርም ሆነ ስናደርግ ነጻነት በሚሰጠው ህግ እንደሚፈረድብን ሰዎች መሆን አለብን። አድልዎ ማድረግ ትተን በሰዎች ላይ ምህረት ማድረግ አለብን። ይህንን ብናደርግ እኛም አይፈርድብንም። መንፈሳዊ ብስለታችን በምናደርገው ድርጊት ይታወቃል፣ይወሰናል።

***መደምደምያ፡***_ስለዚህ እግዚአብሔር ስለማይፈቅድና ከፍርዱ ሥር ስለምንሆን አድልዎ በማንኛውም ቦታ ማድረግ የለብንም። ነገሩን አውቀን ከሆነ አድልዎ የምናደገውም በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ላይ ነው። የፍቅር ሕግም አይፈቅድም። የጌታ መልክና ምሳሌ ባለበት ሰው ላይ ማድላት **ኃጢአት ነው።** ኃጢአትም ሁሉ እኩል ነው።
ሰው ሁሉ እኩ፤ ነው። ገላ 3፡28 የሚከተለውን ብሎ ያረጋግጣል"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና"።ስለዚህ ክርስቲያን በምንም ሳይመካ ሁሉም በጌታ እኩል እንደሆን በማወቅ የአድልዎ ኃጢአትን ማስወገድ አለበት።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1.ያዕቆብ በመልዕክቱ 15 ጊዜ ከተጠቀማቸው "ወንድሞች" ከሚል ቃል በያዕ 2፡1 የተጠቀሰው አንዱ ነው። ይህ ጠቃሚ ቃል ምንን ያመለክታል? ለምንስ ተጠቀሰ? በዚህ ክፍል አድልዎ አታድርጉ ብሎ ሲል ምክንያቶቹ ምንድ ናቸው?

2. ሀ. እንደ እግዚአብሔር ቃል ድሃና ሀብታም ማን እንደሆነ ይብራራ? የያዕቆብ መልዕክት ተቀባዮች የተሳሳቱበት ነጥብ ተወያዩ? ማቴ 5-7 ለተጨማሪ ማብራሪያ ይነበብ። መጻፍ የሚትችሉ በሚገባችሁ ቋንቋጻፉ።

ለ. 2፡2-4 ሲነበብ አንድ ሰው መከበር ወይንም ቦታ መሰጠት ያለበት መመዘኛው ምንድ ነው? ከውጫዊ ነገር ባለጠግነት ይልቅ የእምነት ባለጠግነት ይበልጣል ማለት ምን ማለት ነው?

3. በቁ.4 መሠረት ይህንን አድልዎ የምናደርግ ከሆነ ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆንን ይናገራል? ለምን?

4. ሀ. በያዕ 2፡5-13 ቁ.5 **አድልዎ ማድረግ የሌለብን የጸሐፊው መቃወሚያ ሀሳቦች (ምክንያቶች) ምንድ ናቸው** (በዳኑት ሰዎች መካካል ድሆች መገፋት አያስፈልግም ብሎ ያቀረበው ምክንያት ምንድነው)?

ለ. 2፡6-7 ለባለጠጎች ማድላት እንደሌለብን 3 መከራከሪያ ነጥቦችን ያስቀምጣል። እነዚህ ሶስቱ መከራከሪያ ነጥቦቹን በዝርዝር አስቀምጡ? እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን የሚከተሉ ናቸው ወይንስ አይደሉም? ቢሆኑም ባይሆኑም ምን ለውጥ አለው?

5. 2፡8-13 በዚህ ክፍል መሠረት ኃጢአት ሁሉ አንድ ነው። ከክፍሉ ሀሳብ ጋር ስናያይዝ ምን ማለቱ ነው? ጸሐፊው ለማብራሪያነት የተጠቀመው ምንድ ነው?

6. በያዕቆብ መልዕክት የተጠቀሰው "የንጉስ ወይም ክቡር ህግ" በዘሌ 19፡16፣ሉቃ 6፡20-22 ኢሳ 10፡2 ጋር ምን ይገናኛል? ይህ ህግ ሥራው ምንድ ነው? ያዕ 2፡8 በማቴ 22፡37-40 ከተጠቀሰው ወርቃማው ትዕዛዝ በሰዎች ላይ ከሚደረገው አድልዎ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ተውያዩ

7. እኛስ በቤታችን፣ በአገልግሎታችንና በሥራ ቦታችን እንደዚህ ዓይነት ፈተና ገጥሞን ያውቃል? ምንስ አደረግን? የተሳሳተ አድርገን ቢሆን ከዚህ፡በኋላ ምን ዓይነት ሰዎች መሆንን እንመርጣለን?

***የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት አምስት***
***እምነትና ሥራ***
***ያዕ 2:14-26 (ክፍል ሁለት)***
*እምነትና ሥራ የሚለው ቃል የእምነት ፍሬን የሚያጠቃልል ሐረግ ነው።*

**የጥናቱ ዓላማ፡** በክርስቶስ ያመነውን እምነት በየቀኑ በሥራ የሚገለጥ መሆኑን ማሳሰብና ማስጠንቀቅ።

***መግቢያ***
ያዕ 2:14-26 ትኩረት ተሰጥቶ ከተነበበ አጠቃላይ የመልዕክቱን ጭብጥ ሃሳብ የያዘ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በየዕለቱ በጌታ ያለንን እምነት ሥራ ላይ እንድናውል ያስገነዝበናል፤ያስጠነቅቀናልም። የዚህ ክፍል እምነትን በሥራ መግለጥ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ በተፈጠረውና በጌታ ደም በዳነው ሰው ላይ አድልዎ አታድርጉ ከሚለው ከለፈው ጥናት ጋር ይገናኛል። በርግጥ ይህ ክፍል ተጨማሪ ትምህርቶች ቢኖሩትም እምነቱን በሥራ የሚያሳይ ክርስቲያን አድልዎን በማስወገድ ህይወቱን ማሳየት አለበት። ይህ ክፍል በጥብቅ የሚያስተምረን በእግዚአብሔር መንግስት ሀብታም ነገር ግን በምድራዊ ነገር ድሃ የሆኑትን ሰዎች ካለን በማካፈል እምነታችንን በሥራ ማሳየት አለብን ይሆናል።

1. **2፡14 ጥቅም የሌለው እምነት ዬቱ ነው?** ለኪሳራ ሰው ሲነግድ ገጥሞን ያውቃል? "ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?" ለመልዕክቱ ተዳራሲይን እምነት አለን የሚሉ በተግባር ካልገለጹ ጥቅም የሌለው የኪሳራ እምነት እንደሆነ ያሳስባቸዋል።
**ክርስቲያን በጌታ እምነት መኖሩን በምን ይታወቃል?** ለምሳሌ በአንድ በታሸገ ዕቃ ከላዩ ወርቅ አለበት ተብሎ ቢለጠፍ እና በውስጡ ግን ተቃራን ነገር ቢኖር የማይስማሙ ሁለት ነግሮች ናቸው የሆኑ ማለት ነው። እንደዚሁም ያዕቆብም እያለ ያለው እምነት እውነተኛ ከሆነ ያመነውን ነገር በተግባር መግለጥ መቻል አለበት። ዛፍ የራሱን ፍሬ ባያፈራና ላም በግ ብትወልድ አያስገርምም? ሁሉም ሰው ግራ ሊገባው ይችላል።
2. 2፡15-16 **እምነታችንን በምን እንግለጥ (እንዴት ለሌሎች የሚጠቅም እናድርግ)? መልሱ በአጭሩ በሚቀጥለው ጥቅስ ይገኛል** "ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ከእናንተ አንዱም በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?"። በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ከእኛ እርዳታ ለምሳሌ ልብስ፣ ምግብ፣ሌሎችንም የሚፈልጉ ሰዎችን አይተን እንዳላየን መሆን በሥራ ያልተገለጠ ጥቅም የሌለው እምነት መሆኑን ያረጋግጣል። በዚህ ክፍል ልብስ እና ምግብ እንደምሳሌ ቢጠቀሱም ሰዎች መረዳት ያለባቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ ለሁላችንም እንግዳ ነገር አይደለም። ቁ.17 ይህ የማይሆን ከሆነ እምነችን የሞተ ከምላስ ያላለፈ እንደሆነ ይነግረናል። በመጠን መኖርና በተረፈው ሌሎችን መርዳት እምነትን በሥራ መግለጥ ነው። ንግግራችን ብቻ አይጠቅምም።የሰው ልጅ አሁን ልተንፍስ አሁን ላቁም ማለት እይችልም፡፡እምንትና ተግባር እንደዚሁ ነው።

**3. 2፡18-23 እምነትን ከሥራ ለይተህ አሳየኝ? ይህ ንግግር** የምፀት ንግግር ነው። እምነትንና ሥራን መለየት አይቻልም። ነገር ግን ይህን ከተናገረ በኋላ ድነትን ስለማያስገኘው እምነት ማስተማር ይጀምራል። አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ህልውና አይክዱም ነገር ግን ወደ ህይወታቸው አምነው አያስገቡትም። ይህንን ሲያብራራ ያዕቆብ አጋንንትም አንድ እግዚአብሔር መኖሩን ያምናል፤ ይንቀጠቀጣልም ይላል "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል " (ያዕ2፡19)። ይህ ደግሞ እምነት በሥራ የዋለ እምነት አይደለም። ይህ እምነት ከንቱና(2፡20) ሙት (2፡26) እምነት ተብሎ ተሰይሟል። በርግጥ ሌሎችም ለድነት የማይጠቅሙ የተለያዩ እምነቶች አሉ። ያዕቆብ ይህንን ማብራሪያ የተጠቀመው በጌታ የሚያምን ሰው እምነቱን በሥራና በተግባር ማሳየት እንዳለበት ለማስረገጥ ነው። በጌታ ቤት ያለን እምነትና ሥራ የአንድ ሳንትም ሁለት ገፅታዎች ናቸው። አሁን እምነት አሁን ደግሞ ሥራ ብለን ለያይተን የምናስቀምጠው ነገር አይደለም።
**የመልዕክቱ ጸሐፊ** እምነትን በሥራ የገለጡትን ሰዎች ለማብራሪያነት ከብሉይ ኪዳን ይጠቀማል። ለዚህ ማብራሪያ የተጠቀመው አብርሃምን ነው፡- አብረሃምን እምነቱን በሥራ እንዲገልጥ እግዚአብሔር ጠየቀው። እብርሃምም ልጁን ለመስዋዕት በመታዘዝ አቀረበ (ዘፍ 22)። በዚህም ምክንያት አብርሃምም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ። እኛም ሌሎችን የእምነት አባቶችን መጥቀስ እንችላለን (ዕብ 11፡18-18)። በጌታ ያመነው እምነት በአፋችን ብቻ አዎን አይደለም ከማለት ያለፈ በሥራ የተገበር ህይወት ነው።
4. 2፡24-26 **ሰው ሊጸድቅ የሚችለው በምንድ ነው? እምነትና ጥሩ ሥራ ሰውን ሊያጸድቅ ይችላል ወይስ ሁለቱም? "ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ *ታያላችሁ*"** *ታዲያ* በዚህ ቁጥር መሠረት የዘለለም ህይወት የሚያስገኘ ሥራ ነው ማለት ነው? ይህንንም ለማብራራት ያዕቆብ የተጠቀመው <u>ረዓብን</u> ነው። ታርኳም በኢያሱ 2 ላይ ተጽፎ ይገኛል። እርሷም **<u>በእምነት</u>** ኢያሱ የላካቸውን ሰላዮችን ከሞት አዳነቻቸው። የእምነት ጀግንነቷንም የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊ መስክሯል (ዕብ 11፡18-18፤31)። ልንጠነቀቅ የምገባን ነገር ቢኖር አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች እንደሚሉት ሰው በጎ ነገር ስላደረገ ወደ አግዚአብሔር መንግስት መግባት ይችላል ማለት እውነተኛ ወንጌል አይደለም።
ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሀሳብ ያዕቆብ ሥራ ያድናል እያለ ነው ብለው ለሚያመነቱ ሰዎች መልስ ይሆናል። በርግጥ መልዕክቱ የተጻፈው ህግ ጠባቂዎች ለነበሩና ወደ ጌታ ለመጡ ቢሆንም ሰው ህይወት የሚያገኘው ህግን በመጠበቅ ወይንም የተለያዩ

ደግ ነገሮችን በማድረግ ነው አይልም። ነገር ግን ዋና መልዕክቱ ያመነውን ነገር በሥራ እንግለጥ ነው። ያዕቆብ በሥራ የዘላለም ህይወት ይገኛል ብሎ አያምንም። ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ ምዕራፍ 15 እንደሚነግረን ሰው በመገርዝና ሌሎች የሙሴ ህግን በመጠበቅ ሳይሆን የዘላለም ህይወት የሚያገኘው በጌታ በማመንና ቀጥሎ ያለውን ትዕዛዝ በማድረግ ነው "ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ" (ሐዋ 15፡28-29) ብለው በኢየሩሳሌም ከተስማሙ መሪዎች አንዱ ነው።

አንዳንዶች ሐ/ጳውሎስ ሥራን ሳይሆን እምነትን ብቻ ነው የሚሰብከው ብለው ቢናገሩም ከያዕቆብ መልዕክት ጋር የሐ/ጳውሎስ አቋም እይጋጭም።ለምሳሌ ኤፌ 4-6፣ ሮሜ 12-14፣ 1ቆሮ 13 እና ሌሎችንም ብናይ እምነታችንን በተግባር ማሳየት እንዳለብን ያስተምራናል። ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን መልዕክቶችን በሙሉ እይታ ማየት እንዳለብን ነው። ጌታም "የተራራው ስብከት" ተብሎ በሚታወቀው (ማቴ 5-7) ጠንከር ባለ መልኩ ያስተማረው እምነትን በሥራ እንድንገልጥ ነው። በሉቃ 10፡36-37 የተጻፈው የደጉ ሳምራዊ ትምህርትም ይህንኑ ያጠናክራል። ያዕቆብ በዚህ ምዕራፍ መደምደሚያው ላይ እንዲህ በማለት ይዘጋል "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" (2፡26)። የሞተ ነገር ይዘን መኖር እንፈልጋለን? መልሳችሁ ግልጽ ነው፡፡ ታዲያ ዛሬ እንነሳ።

***መደምደምያ፡***

ክርስቲያን ያመነውን እምነት የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያዘው መሠረት በሥራ ማሳየት አለበት። "ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ከእናንተ አንዱም። በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?" (ያዕ 2፡15-16)። አማኝ እምነቱን በሥራ ካልገለጠ ፍሬ እንደሌለው ዛፍ ወይንም የራሱን ሳይሆን ሌላ ፍሬ እንደሚያፈራ ዛፍ ነው። እምነትና ሥራን ገነጣጥሎ ማሳየት አይቻልም። ደግ ሥራ ያለ ክርስቶስ እምነት በርግጥ አያድነንም። በተጨማሪ የሉቃስ 10፡29 ጥያቄ ራስዎን ይጠይቁ "...ባልንጀራዬስ ማን ነው..." ። መልሱ በመንገድ ላይ ወድቆ ወይንም በተለያዩ ችግሮች እርዳታ የሚጠይቅ እና የምትጠይቅ እህት ናቸው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በያዕ2፡14 መሠረት ጥቅም የሌለው እምነት የቱ ነው? ጥቅም ያለውስ?

- ክርስቲያን በጌታ እምነት መኖሩን በምን ይታወቃል?

2. በያዕ2፡15-17 ላይ የመልዕክቱ ጸሐፊ እምነትን በሥራ ግለጡ ብሎ የተጠቀመው ምሳሌ ምንድ ነው?

- የጠቀሳቸው የሰው ልጆች ፍላጎቶችስ ምንድ ናቸው?
- ከነዚህ ሌሎች ሰዎችን መርዳት ያለብን ነገሮች አሉ? ምን?

3. በያዕ2፡18-20 በእግዚአብሔር አጋንንትም ያምናል፣ይንቀጠቀጥማል የሚለው "እምነት" ምን ዓይነት እምነት ነው?

- እንደዚህ ዓይነት እምነት እንዳይኖረን ብሎ የሚመክረን ለምንድ ነው?

4. በያዕ2፡21-23 ያዕቆብ እምነት ያለ ሥራ የሞተ መሆኑን ለማሳየት ሁለት የብሉይ ኪዳን ማብራሪያ ምሳሌዎችን ተጠቅሟል። እነማን ናቸው?

- ከነዚህ ምሳሌዎች ሌላ መጥቀስ ይቻላል? እነማንን? ምን አደረጉ? (የዕብራዊያንን መልዕክት 11)።

5. በያዕ 2፡24-26 ትኩረት መሠረት እምነትና ሥራ በምን ይገናኛሉ? በምንስ ይለያያሉ? መለያየት ይቻላል ወይስ አይቻልም? ቁ.26ን ተነጋገሩ።

6. ጥሩ ሥራ ሰውን ሊያጸድቅ ይችላል? ካልሆነ ምን ያስፈልገናል? አይደለም ወይም አዎን ካልክ ምን ማስረጃ አለህ? ያዕቆብ በሐዋ 15 የኢየሩሳሌም ጉባኤ ውሳኔ ምን አቋም ነበረው?

7.ታዲያ ይህንን የእግዚአብሐርን ቃል ወይይት እንዴት ሥራ ላይ እናውል።

- አሁን እምነትን በሥራ የምንገልጽበት መንገድ አለ? እንዴት?

***የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ስድስት***
***አንደበትን መግራት***
***ምዕራፍ ሦስት - (ክፍል አንድ)***

***የጥናቱ ዓላማ፡*** አንደበትን አለመግዛት የሚፈጥረውን አደጋ በማስተዋል አንደበታችንን እንድንገዛ ማሳሰብ።

***መግቢያ***
የያዕቆብ መልዕክት እምነታችንን በተግባር እየገለጥን እንድንኖር የሚያስተምር መጽሐፍ እንደመሆኑ መጠን፣ በዚህ ምዕራፍ አካሄዳችንን እንደ አማኝ ልንገልጽበት የሚገቡንን ሁለት ነገሮች ማለትም አንደበትን መግዛት እና ኑሮአችንን በሰማያዊ ጥበብ እንድንመራ ያስተምራል። በዛሬው ጥናታችን ያልተገራ አንደበት ሊፈጥር የሚችለውን አደጋ በመረዳት አንደበታችንን መግዛት እንዳለብን እናጠናለን። ስለ ሰማያዊው ጥበብ የሚናገረውን ግን በሚቀጥለው ጥናት እንመለከታለን።

1. ***ሁሉ ሰው በአንደበት ይሰናከላል*** (1-2)

በቁ. 1 ላይ እንደሚያመለክተው፣ ያዕቆብ በዚህ ክፍል ላይ ሊያተኩር የፈለገው "**አስተማሪዎች**" ላይ ነው። አስተማሪዎች በሚያስተምሩት ቃል ሊፈረድባቸው ስለሚችሉ ብዙዎች አስተማሪዎች ሊሆኑ እንደማይገባ ያሳስባል - በሚያስተምሩበት አንደበት ስለሚጠመዱ ደግሞም አንደበትን መግዛት አስቸጋሪ ስለሆነ ማለት ነው። በተለያየ ነገር የተለያየ ሰው መሰናከሉ የተለመደ ቢሆንም፣ በአንደበት መሰናከል ግን፣ አስተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ "***ሁላችንም***" እንሰናከላለን ቁ.2።

2. ***ትንሹ አንደበት ታላቁን የሰው ሁለመና ሊመራ ይችላል*** (3-5)

ምላስ/ አንደበት ትናንሽ ከሆኑት ከሰውነት የአካል ክፍሎች አንዱ ነው። ሆኖም ግን መላ ሰውነትን፣ መላ የሕይወት ጎዳናን ሊመራ የሚችል ነገር ነው። ይህንን ለማስረዳት ያዕቆብ ከቁ. 3-5 ሁለት የፈረስ ልጓምን እና የመርከብ መቅዘፊያን ምሳሌ አድርጎ ይሰጣል። "***ፈረሶች***" ምንም ትልቅ አና ጉልበታም ቢሆኑ፣ በትንሽዬ "**ልጉዋም**" ወደ የት መሔድ እንዳለባቸው ይመራሉ እንዲሁም ይገራሉ። ልክ እንዲሁ፣ "**መርከቦች**" እጅግ ትልቅ መጓጓዣ ቢሆኑም፣ ሊሄዱበት የሚገባው አቅጣጫ ግን የሚመራው፣ በትንሽ "***መቅዘፊያ***" ነው። አንደበትም እንዲሁ ነው! "እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል።" (ቁ. 5) ወይም በሌላ አባባል መላስ ምንም እንደ ልጓም እና እንደ መቅዘፊያ ትንሽ ቢሆንም ታላቁን የሰውን ሁለ መና በመልካም ሊመራ እና ሊያጠፋ የሚችል ነገር ነው።

3. ***ትንሹ አንደበት ካልተገራ ታላቅ አደጋ ያስከትላል*** (5-6)

አንደበት መላ ሰውነትን እና ሕይወትን በመልካም ሊመራ የሚችል መልካም ነገር ቢሆንም ፣ በትክክል ካልተያዘ አደገኛ እና መላ ሕይወትን ሊያበላሽ የሚችል ነገር ነው። ያዕቆብ እንደገና የዚህን እውነት ለማስጨበጥ እሳትን ምስሌ አድርጎ ያቀርባል። "**እሳት**" ጠቃሚ እና አስፈላጊ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ሆኖም ግን በአግባብ ካልተያዘ "እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል።" (ቁ. 5)።

4. ***አንደበት ምንም ወላዋይ ቢሆን በአማኞች ዘንድ ግን የተገራ እና ወጥ እንዲሆን ይገባል*** (7-12)

በአጭሩ አንደበት ጠቃሚ ነው ግን በአግባብ ካልተያዘ አደገኛ እና አጥፊ ነገር ነው። ሆኖም ግን አንደበትን ሙሉ በሙሉ መግዛት አስቸጋሪ ነው። ለዚህ ነው ያዕቆብ ገና በቁ. 2 ላይ "ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና፤ በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው።" ማለቱ። ሰው ምንም ፍጥረታትን ቢገዛና ቢያስተዳድር፣ አደበትን ግን ፈጽሞ መግዛት ለሰው አስቸጋሪ ነገር ሊሆን ይችላል ቁ 7-8። ለዚህም ነው ሰው አንዴ በአንደበቱ እግዚአብሔርን ሲባርክ በዚያው አንደበቱ የማይገባ ተናግሮ ራሱን በማርከስ ሲወላውል የሚገኘው (ቁ. 9)።

ስለዚህም ያዕቆብ በዚህ ክፍል የክርስቲያን አንደበት ወጥ ሊሆን እንደሚገባ ያሳስባል (ቁ 10-12)። ተፈጥሮን እንኳ ስንመለከት በተፈጥሮ ውስጥ ወጥነት (consistency) እናያለን። ለምሳሌ ከአንድ ምንጭ በአንድ ጊዜ የሚጣፍጥ እና መራራ ውሃ አይወጣም። አንድ ምንጭ የሚሰጠው ወይ መራራ ውሃ ነው አልያም ጣፋጭ ውሃ ነው። ልክ እንዲሁ የበለስ ዛፍ ሌላ ፍሬ አታፈራም፣ የብርቱካን ዛፍ ሙዝ አይሰጥም! ክርስቲያንም እንዲሁ ከአንደበቱ የሚወጣው ወጥ የሆነ መልካምነት እንጂ፣ አንድ ጊዜ "**ጌታን እና አብን**" እየባረክን ሌላ ጊዜ "**እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች**" ልንረግም ከቶ አይገባም። የክርስቲያን አንደበት ጳውሎስ በቆላስይስ መልዕክቱ እንዳሳሰበው "**ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ፥ በጸጋ ይሁን**" (ቆላ 4፡6)።

***መደምደምያ፡*** አንደበት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው መልካም ስጦታ ነው። በሚገባ ሊያዘው፣ አንደበት ሰውን ወደ መልካም ጎዳና ሊመራ፣ ሰውን ሊያከብር እና ሊያለማ የሚችል ነገር ሲሆን፣ አንደበቱን መግዛት ላቃተው ግን ትንሽ እሳት አገርን ሊያጠፋ እንደሚችለው ሁሉ የሚያጠፋ ነው። ስለዚህም ክርስቲያን አንደበቱን ሊገዛ ይገባል። ያዕቆብ በመልዕክቱ አንደበታችንን የምንጠቀመው፣ ወጥ በሆነ መልኩ እንደ እግዚአብሔር ቃል በመልካም እንድንጠቀምበት እንጂ፣ አንዴ ለአለማዊነት ሌላ ጊዜ ለመልካም እየተጠቀምንበት እንዳንወላውል ያሳስባል።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

1. ቁ.1 የሰው አንደበት የተናጋሪውን ሕይወት ሊያጠፋ እና ሊያለማ የሚችለው እንዴት ነው? ምሳሌ መስጠት ትችላለህ?

2. በቁ. 2 ላይ እና በቁ. 8 ላይ ያለውን በመመልከት፣ የሰው ልጅ አንደበቱን መግዛት አይችልም ማለት ነው?

   - መግዛት አይችልም ማለት ከሆነ፣ ያዕቆብ የማይቻል ነገር እየመከረ ነው ማለት ነው?

3. በዚህ ክፍል ውስጥ (ያዕ 3፡1-11) የአንደበትን ታላቅነት፣ አደገኝነት፣ እንዲሁም እንዴት ወጥ መሆን እንዳለበት ለማስረዳት የተለያዩ ምሳሌዎች ይሰጣል።

   - የተሰጡት ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

   - የአንደበትን ታላቅነት፣ አደገኝነት እና ወጥ በሆነ መልኩ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት እነዚህ ምሳሌዎች የሚያስረዱት እንዴት ነው?

4. በቁ. 8 ላይ አንደበት "ወላዋይ ክፉት ነው" ይላል። ያዕቆብ አንደበትን ወላዋይ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? (ቁ.9-10) ያለውን ያነጻጽሩ።

5. ሰው አንደበቱን ይገዛል የሚባለው መቼ ነው? (ዝም ሲል ነው? ሲቆጣ ነው? ... አንደበትን የመግዛት መለኪያው ምንድን ነው ብለህ ታስባለህ)?

6. አንደበትን ወጥ በሆነ መልኩ መጠቀማችንን የሚያመለክተው ምንድን ነው? ቁ 11ን ልብ ብለው ይመልከቱ።

7. ምሳ 16፡1 እንዲሁም ቆላ 4፡6ን በመመልከት አንደበትን በሚገባ ልንጠቀምበት የምንችልበትን ምን መንገዶች ይሰጣል?

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ሰባት**
**በኑሮ የተገለጠ ሰማያዊ ጥበብ**

***ምዕራፍ ሦስት* - (ክፍል ሁለት)**

**የጥናቱ ዓላማ፡** እንደ እግዚአብሔር ቃል መመላለስ ጥበብ መሆኑን በመረዳት እንደ ጥበበኞች እንድንመላለስ ማሳሰብ!
***መግቢያ***
በጥበብ መመላለስ እና ጠቢብ መሆንን ሁሉም የሚፈልገው እና የሚመኘው ቢሆንም፣ ሰዎች ስለ ጥበብ ያላቸው መረዳት ግን እጅግ የተለያየ ነው። ለአንዳንዱ ነውር፣ አጭበርብሮ ማግኘት ጥበብ እና አራድነት እደሆነ ሲያስብ፣ ሌላው ቅንነትን እና ታማኝነትን እንደ ሞኝነት ይቆጥራል። ያዕቆብ ግን በዚህ መልዕክቱ እውነተኛ እና ሰማያዊ ጥበብ ምን እንደሆነ በማስገንዘብ በኑሮአችን እውነተኛ ጠቢባን እንድንሆን ይመክራል። በዛሬው ጥናታችን፣ በጽድቅ በመኖር እውነተኛ ጠቢባን መሆን እንዳለብን እንማራለን።

1. **ጥበብ የሚገለጸ በኑሮ ነው! (3፡13)**

ያዕቆብ በዚህ ክፍል (ያዕ 3፡13-18) ባለው ክፍል ሦስት ነገሮችን ያስጨብጠናል። የመጀመሪያው የሚያሳስብን ነገር ጥበብ በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደሚታሰበው፣ የአዕምሮ ጉዳይ ወይንም የአስተሳብ ችሎታ ሳይሆን፣ ጥበብ የኑሮ ጉዳይ እንደሆነ ነው። በቁ. 13 ላይ "**ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው?**" ብሎ ለሚጠይቀው ጥያቄ ብዙዎች ጥበበኞች እንደሆኑ ያስቡ ይሆናል። ሆኖም ግን ጥበብ የሚታየው "**በመልካም አኗኗር**" እና ከጥበብ በሚገኝ "**የዋህነት**" ወይንም ትህትና ነው።

2. **ምድራዊ ጥበብ እና ውጤቱ (3፡14-16)**

የሰው ጠባብነት የሚለካው ምንም እንኳ በአኗኗር ቢሆንም፣ የሰው አኗኗር ደግሞ ሁለት አይነት ጥበቦች መኖራቸውን ያሳያል - ምድራዊ ጥበብ እና ሰማያዊ ጥበብ። ከቁ. 14-16 ባለው ክፍል ምድራዊው ጥበብ ምን እንድሆነ በሚገባ ይስረዳል። ምድራዊ ጥበብ የሚገለጠው በአኗኗር ነው። ሰው በልቡ ክፉ አሳብ፣ "***መራራ ቅንዓት***" እና "**አድመኝነት**" ካለበት፣ ያ ሰው ትልቅ ጥበብን እንዳተረፈ አድርጎ ሊመካ አይገባም። ወይንም ደግሞ የማያስመካ ክፉ ምኞት እና አድራጎት መሆኑን ሊክድ ወይንም ሊዋሽ አያስፈልግም። በመሰረቱ፣ በክፋት፣ በተንኮል፣ እንዲሁም በማጭበረበር መኖር እንደ ብልህነት ተቆጥሮ፣ የሚመኩበት ሰዎች ቢኖሩም ግን ይህ ራስን ማታለል እና ራስን መዋሸት ነው።

ያዕቆብ ሰው በዚህ አይነቱ ጥበብ ለምን መመካት እንደሌለበት ሲያስረዳ፣ እንዲህ ያለው "**ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤**" (15) ይለናል። ይህ ጥበብ አንደኛ ምድራዊ ነው። መንፈሳዊ ወይንም ሰማያዊ ባለመሆኑ፣ የዚህ ጥበብ ትርፉ ለምድራዊ ነገር ብቻ ነው። ሰው መንፈሳዊ ሕይወት የሚያተርፍለት ነገር አይኖርም። ሁለተኛ የሥጋ ጥበብ ነው ምክኒያቱም ለክርስቶስ እንድንኖር ይሚያደርግ ጥበብ ሳይሆን እንዲህ ያለው ጥበብ የሥጋ ምኞትን ብቻ ለማርካት የሚጠቅም ነው። በሦስተኛ ደረጃ የአጋንንት ነው ምክኒያቱም የዚህ አይነቱ ጥበብ ምንጭ ዲያቢሎስ ነውና። ቅንዓት፣ አድመኝነት፣ የሥጋ ስራዎች እና ክፉ ድርጊቶች ሁሉ የበረከት ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሚወርድ አይደለም።

በቁ. 16 ላይ የዚህ አይነቱ ጥበብ ትርፉ እና ውጤቱ ምን እንደሆነ ያስገነዝበናል - "**ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና**" (ቁ. 16) ። ቅንዓት እና አድመኝነት ሰማያዊ ወይንም መንፈሳዊ ጥበብ ሊሆኑ የማይችሉበት ምክኒያት ምድራዊ፣ ሥጋዊ እንዲሁም አጋንንታዊ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ትርፉ "**ሁከት እና ክፉ ስራ**" ነው። እግዚአሔር ግን የሁከትም ሆነ የክፉ ስራ ምንጭ ስላይደለ እንደዚህ አይነቱን እኩይ ድርጊቶች የሚያተርፍ ጥበብ ከእግዚአብሔር ሊመጣ ከቶ አይችልም።

3. **ሰማያዊ ጥበብ እና ውጤቱ (3፡17-18)**

ታዲያ ሰማያዊው ጥበብ እንዴት ያለ ነው ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ያዕቆብ በቁ. 17 እና 18 ላይ ለዚህ መልስ ይሰጣል። "**ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት**" (ቁ. 17)። መንፈሳዊው ወይንም ሰማያዊው ጥበብ፣ እንደ ምድራዊው ተንኮል እና ክፋት ሳይሆን፣ "**ንጽሕና**" የሞላባት፣ ከሁከት እና ከጥል ይልቅ እርቅን እና ገርነት የሞላባት፣ ከአድመኝነት ይልቅ ምሕረትን የምትመርጥ ናት። በሌላ አባባል ሰማያዊው ጥበብ በ ገላ 5፡22-23 ላይ የተለገጸውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የምታፈራ ናት። ያዕቆብ ይህንን ጥበብ "**የላይኛይቱ ጥበብ**" ብሎ ይጠራታል ምክኒያቱም እንዲህ ያለው ጥበብ "ከላይ ከብርሃናት አባት" የሚወርድ ነውና።

በቁ. 17 ላይ ይህንን ጥበብ ለሚከተሉ ሰዎች የሚያገኘውን ውጤት ይነገረናል። እንደ ሰማያዊው ጥበብ መሰረት "ሰላምን በመፍጠር በሰላም ለሚዘሩ ሰዎች" የጽድቅን ፍሬ ያስገኝላቸዋል። ይህ አይነቱ ጥበብ ባለበት የሚገኘው፣ እንደ ምድራዊ ጥበብ ሁከት እና ክፉ ስራ ሳይሆን፣ ሰላም እና ጽድቅ ነው።

***መደምደምያ፡***
መጽሐፍ ቅዱስ ክፋትን፣ ተንኮልን እንዲሁም እግዚአብሔራዊ ባልሆነ መንገድ የሚደረጉ ነገሮችን እንድናደርግ መቼም መክሮ አያውቅም። ነገር ግን በጥበብ እና እግዚአብሔርን በመፍራት ግን ሁሌም ይመክራል። ስለ ጥበብ ስናነሳ፣

እውነተኛው እና ሰማያዊው ጥበብ በመልካም አኗኗር የሚገለጠው ጥበብ ነው። ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ “የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው” (ምሳ 1፡7) ሲል እውነተኛው ጥበብ እግዚአብሔርን በመፍራት የሚደረግ ነገር እንጂ በከፋት እና በልብ ጠማምነት የሚሰራ ነገር እንዳልሆነ ያሳስበናል። ስለዚህም ዛሬ እውነትኛ በሆነ ጥበብ ለመመላለስ የምናስብ ከሆነ እግዚአብሔርን በመፍራት እና በጽድቅ እንድንኖር የእግዚአብሔር ቃል ያዛል።

***የመወያያ ጥያቄዎች:***

1. 3፡14-16 በዚህ ክፍል መሰረት፣ ስንት አይነት ጥበቦች አሉ? ልዩነታቸውስ ምንድን ነው?

2. 3፡13 የሰው ጥበበኝነት የሚለካው በምንድን ነው?

3. ባለፈው ጥናታችን ስለ አንደበት ተነጋግረን ነበር። በጥበብ መኖር እና አንደበትን መግዛት የሚያገናኛቸው ነገር ይኖራል ብለህ ታስባለህ? አዎን ካልክ እንዴት?

4. ያዕቆብ እምነትን በሥራ ማሳየት እንዳለብን የሚናገር መጽሐፍ እንደመሆኑ፣ በጥበብ መመላለስ እና እምነትን በስራ ማሳየት የሚገናኙት እንዴት ነው?

5. 3፡15 ስለ ምድራዊ ጥበብ ሲናገር “ የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው” ነው ይላል።

   - የምድር የተባለው ለምድን ነው

   - የሥጋ ነው የተባለውስ ለምድን ነው?

   - የአጋንንት የሆነውስ ለምንድን ነው?

6. 3፡16 ምድራዊ ጥበብን በመከተል የሚገኘውን ውጤት በገላ 5፡19-21 ላይ ከተዘረዘረው የሥጋ ሥራ በምን ይገናኛል?

7. ሰማያዊውን ጥበብ፣ እየደጋገመ “ከላይ” እንደሆነ ይናገራል (ቁ. 15 እንዲሁም 17)። ከላይ የሚወርድ ጥበብ ሲል ምን ማለቱ ነው። (ከምድር የሆነ ጥበብ እና ከላይ የሚወድ ጥበብ የሚሉትን አሳቦች አወዳደር)።

8. ሰማያዊው ጥበብ በገላ 5፡22 ላይ ከተዘረዘሩት የመንፈስ ፍሬዎች ጋር በምን ይገናኛል? ውጤቱስ ምንድን ነው?

9. ምሳ 1፡7 “እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው።” ሲል እግዚአብሔርን መፍራት የየትኛው ጥበብ መጀመሪያ ነው? እግዚአብሔርን መፍራት የምድራዊው ጥበብ መጀመሪያ ያልሆነው ለምንድን ነው?

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ስምንት**
**የጥል ምንጩ (የጥል ምክንያት)**

**የምንባብ ክፍል፡ 4፡1-10**

**የጥናቱ ዓላማ፡** *ምንም እንኳን በመካከላችን አንዳንድ ጊዜ መጣላት ቢኖርም ጠላታችን ወንድማችን ወይም እህታችን ሳይሆኑ የገዛ ስጋችን፥ አለምን መውደድ፥ሰይጣንና ሃጢአት እንደሆኑ ለማሳየት ነው።*

***መግቢያ፡*** *በአማኞች መካከል መጣላት ሊኖር ይችላል። ከመጣላት ነፃ ላንሆን እንችላለን። ጥሉም ቀላል ጥል ሳይሆን የመረረና እንደ ጦርነት የከበደ ሊሆንም ይችላል። ሆኖም ግን የጥላችንን ምክንያት ቆም ብለን በመፅሐፍ ቅዱስ ዓይን ብናየው ወደ ጦርነቱ የሚያስገባን የገዛ ስጋችን፥አለምን መውደዳችን፥ ሰይጣንና ሃጢአታችን መሆናቸውን እናያለን። ይህንን ማወቃችን ጉልበታችንን ወደ እውነተኛው ጠላታችን እንድናዞር ይረዳናል። ያዕቆብ በዚህ ክፍል አማኞች እርስ በእርሳቸው ከመጣላት ይልቅ ሥጋቸውን እንዲገዙ፥በአለም ፈንታ እግዚአብሔርን እንዲወዱ፥ሰይጣንን እንዲቃወሙ እና እራሳቸውን ከሃጢአታቸው እንዲያነፁ ይነግራቸዋል።*

**ቁ. 1–3 ስጋ**

4፡1 "በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን" በ"እናንተ" ሲል ስለ አማኞች ብቻ እያወራ እንዳለ ያሳያል። ጦርና ጠብ በአማኞች መካከል አለ። የያዕቆብ ጥያቄ እንዴት ሊኖር ቻለ አይደለም። ነገር ግን ምንጩ ምን እንደሆነ ሊያሳያቸው ይወዳል። ለጥያቄው መልስ አንዳንዶች የጥላቸው ምንጭ እገሌና እገሊት ናቸው ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን ያዕቆብ ዓይናቸውን ከወንድሞችና ከእህቶች እንዲያነሱ ይነግራቸዋል።

*የመጀመሪያውና ዋነኛው የጥል ምንጭ በኛ ውስጥ ያለ ስጋ የተባለ አሮጌው ማንነታችን ነው። በብልቶቻችሁ ውስጥ የሚዋጉ ሲል ስጋችን በውሳጥችን ካለው ከእግዚአብሔር መንፈስ ድምፅ ጋር ያለውን ትግል ነው (ገላትያ 5፡ 15–17 ተመሳሳይ ነገር ይናገናል)። ምኞቶቻችሁ ማለት በውስጣችን የያዝነው ጠንካራ ፍላጎት ወይም ስሜት ነው። ይህ ፍላጎት ደግሞ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሳይሆን ወደ ሃጢአት የሚቸኩል የራሳችንን ነገር ብቻ ለማድረግ የሚጓጓ ስሜት ነው።*

*ይህን ፍላጎት ከግብ ላማድረስ አጥብቀን እንመኛለን። ነገር ግን ምኞት ብቻውን የፈለግነውን ለማግኘት አያስችለንም። ይህ አልሆን ሲል እኛ የፈለግነው ነገር ያላቸውን ሰዎች እንገላለን ወይም እንቀናባቸዋለን። ይህም ደግሞ አይረዳንም። መግደል ሲያቅተን ወደ ጥል፥ክርክር፥ውጊያ ወይም ጦርነት እንሄዳለን።*

*የዚህ ችግሩ የፈለግነውን ለማግኘት አለመስራታችንና ደግሞ ሁሌ ስራ ብቻ ስለማይረዳ ዋና ሰጪ የሆነውን እግዚአብሔርን አለመጠየቃችን ነው። ደግሞ እግዚአብሔርን እንዳንጠይቀው ጥያቄአችን ድፍረት ያሳጣናል። ጥያቄአችንን ከማስተካከል ይልቅ ህሊናችንን አደንድነን ስንጠይቀው ደግሞ እርሱ እምቢ ይለናል። የሚበጀንን እንጂ የሚያጠፋንን አይሰጠንም።*

*በክፉ ትለምናላችሁ ሲል ጥያቄውን የምንጠይቅበት ልብ (motive) ትክክል ስላልሆነ ነው። ይህን ትክክል ያልሆነውን ልብ በምኞቶቻችን መከፈል ይለዋል። በምኞቶቻችሁ ትከፍሉ ማለት ከጌታ የምንቀበለውን ነገር በውስጣችን ያለውን ክፉ ምኞት ለማርካት (ለምሳሌ፡ ሌላን ሰው ለማስቀናት፥ለማታለል ወዘተ ለመሳሰሉ) መጠቀም ማለት ነው።*

**ቁ.4–6 አለምን መውደድ**

ከስጋችን ጋር የተያያዘ ሌላኛው እውነተኛው ጠላታችን አለምን ወውደድ ነው። አለም ሲል ሰማይና ምድሩን አይደለም። አንደኛ የዮሐንስ መልዕክት 2፡15–16 እንዲህ ይላል፥ "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። " ስለዚህ ዓለም ማለት ትምክህተኝነት የገንዘብ ፍቅር፥ ስለሚያስፈልገን ሳይሆን ዓይናችን ስላየው ብቻ ከእግዚአብሔርም ከሌሎችም ሰዎች ጋር ቢያጣላኝም ያንን መምረጥ ነው። በትዳር ጓደኛ ለይ ሌላ መውደድ ጥል እንደሚያመጣብን እግዚአብሔርን ታምነን አለምን መውደድ ከእግዚአብሔር ጋር ያጣላናል። ከእርሱ ጋር የተጣላ ደግሞ ከሁሉ ጋር ይጣላል።

*በዚህ ምድር ስንኖር ስጋና አለምን እንድናሸንፍ የሚረዳንን መንፈስ እግዚአብሔር በውስጣችን አስቀምጦአል። ይህ መንፈስ ግን የሚረዳን በፈለግነው መጠን ነው። ፍላጎታችንን ደግሞ የሚያየው ምን ያህል ሥጋንና የአለምን ነገር እንደምንጠላ ሲያይ ነው። ስለዚህ ትዕቢትን ሲያይ ይቃወመናል። ይህ ማለት ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ተጣላን ማለት ነው። ከእርሱ ጎን መሆን እንጂ ከእርሱ ጋር መጣላት አይበጀንም። ትሁት ሰው ድካሙን አውቆ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ የሚፈልግ ሰው ነው። ለእንዲ አይነቱ ደግሞ ጸጋ ይሰጠዋል። ቲቶ 2፡13–14 እንደሚናገረው ጸጋ የሚሰጠው በውስጣችን ያለውን የሃጢአት ፍላጎትና አለም የምትጋብዘንን ግብዣ እንቢ እንድንል ሊረዳን ነው እንጂ ይህን ክፉ ምኞት ሊያሟላልን አይደለም።*

**ቁ.7–8 ሰይጣን**

አለምንና ስጋን እየተጠቀመ በመጀመርያ ከእግዚአብሔር ጋር ከዛም ከራሳችንና ከሌሎች ጋር እንድንጣላ የሚያደርገው ዋናው ጠላታችን ሰይጣን ነው። ስለሰይጣን አንድ መስመር ብቻ ነው የተጻፈው። ይህም አብዛኛውን ጊዜ ሰይጣንን መከሰሳችን ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳይደል ያሳየናል። ሰይጣንን የምንዋጋው ሲፈትነን በመቃወው ነው። መቃወም ሲል እምቢ ብሎ መገዳደር ማለት እንጅ በኢየሱስ ስም ብሎ መገሰፅ ብቻ አይደለም። ይህን ማድረግ ትክክል ስላልሆነ ሳይሆን፥ ሰይጣን ሊፈትን እንጂ ሊያስገድድ ስለማይችል እምቢ ማለት ብቻ ይበቃዋል ለማለት ነው።

ሰይጣንን እምቢ ደግሞ የምንለው እግዚአብሔርን እሺ ማለት ስንችል ነው። ስለዚህ የመዋጊያው ዘዴ እግዚአብሔርን መቅረብ ነው።

ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል ሲል እግዚአብሔር ያለፈቃዳችን ምንም እንደማያደርግ፥ የኛን ፈቃደኝነት እንደሚጠብቅ ያሳያል።

**ቁ.8–10 ሃጢያት**

ከሌሎች ጋር መጣላታችን፥ የስጋችንን ፍላጎት ማድረጋችን፥ አለምን መውደዳችንና ከእግዚአብሔርም መራቃችን አንዳንዴ አይቀርም። ይህ ደግሞ ሃጢያት ይባላል። እግዚአብሔር እንደዚህ እንደምንበድለው ስለሚያውቅ ልቡ ሰፊ ነው። የልጁንም ደም ለኛ አዘጋጅቶልናል። ነገር ግን ሁል ጊዜ ሃጢያት ሞትን ሳትወልድብን ቶሎ ቶሎ ንስሃ ልንገባ ይገባናል። ዝም ብሎ ይቅር በለኝ ማለት ብቻ ሳይሆን ግን፥ ልባችንና እጃችን እስኪነጻ ድረስ አጥብቀን ጌታን ልንፈልግ ይገባናል። ምንም እንኳ የዳንን ብንሆንም ሃጢአተኞች ነን። ስለዚህ እናንተ ሃጢአተኞች ይላል።

***መደምደምያ፡*** ስለሌሎች ምንም አይናገርም ስለ ሰይጣን አንድ መስመር ብቻ። አብዛኛው የሚያወራው ስለእኛ ነው። አይናችንን ከሌሎች ጥፋት ላይ አንስተን ወደራሳችን እናድርግና በውስጣችን ያልውን የስጋ ምኞት፥የአለም ፍቅር፥ እነዚህ የሚጠቀመውን ሰይጣን እይተዋጋን ሃጢያት ስንሰራ ቶሎ ቶሎ በንስሃ ራሳችንን እናጽዳ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1) ቁ.1 ላይ ጦርና ጠብ የሚለው ስለምን ዓይነት ጦርና ጠብ ነው የሚያወራው?
   ከወዴት ይመጣሉ ብሎ ጠየቀ እንጂ አማኝ ሆናችሁ ለምን ትጣላላችሁ አለማለቱ ምን ያስተምራል?

2) ከቁጥር 2 እስከ 3 የጥል ምንጬ ምንድን ነው  የሚለው?
   ሀ. ምኞቶቻችሁ ማለት ምንድን ነው?
   ለ. የተመኙትን ማግኘት የማይቻለው ለምንድን ነው?
   ሐ. በዚህ ክፍል አማኞች ይገላሉ ማለት ምን ማለት ነው? (በስጋ ይገላሉ ማለት ባይሆንም በምንናገረውና በምናስበው ሃሳብ የአንድን ሰው ሞት ስንመኝ ማለት ነው?)።
   መ. መመኘት ወይም መግደል ሳይሳካ ሲቀር ሌላ አማኞች የሚያደርጉት ምንድን ነው?

3) ከቁጥር 4 እስከ 6 ባለው ውስጥ ሁለተኛው የጥል ምንጭ ማነው?
   ሀ)  አለምን መውደድ ከእግዚአብሔር ጋር ለምን ያጣላል? ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ከሌሎች ጋር ከመጣላት ጋር ምን ያያይዘዋል?
   ለ) መንፈስ ቅዱስ በውጣችን ያለው ለምንድን ነው? ምን ስናደርግ ነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምንጣላው?
   ሐ) ጸጋ የሚሰጠን ለምንድን ነው?

4) ቁጥር 7 ላይ ስለ ሰይጣን ምን እንማራለን?
   ሀ) ስለስጋ ስለዓለም ብዙ ተጽፎ ስለሰይጣን ትንሽ መጻፉ ምን የሚያሳየን ነገር አለ? ምን የተለየ ነገር ተረዳህ?
   ለ) ሰይጣንን እንዴት ነው የምንዋጋው? (ተቃወሙ ማለት በአፋችሁ ገስጹ ማለት ሳይሆን ሃጢአት ሲጋብዛችሁ እምቢ በሉ ማለቱ ነው።)
   ሐ) እግዚአብሔር እኛ ስንቀርበው ብቻ የሚቀርበን ለምንድን ነው? (ሳንድን በፊት እርሱ ሳንፈልገው ፈልጎናል። ግን ከዳንን በኋላ የኛን ፈቃደኝነት ይፈልጋል?

5) 4፡8-10 ሃጢአተኞች የሚለው ማንን ነው? የዳነ ሰው ሃጢአተኛ ነው ማለት ነው?
   ሀ) በዚህ ክፍል መሰረት ምን ዓይነት ሃጢአት ነው አማኝ የሚሰራው? (የስጋ ፍላጎቶችን ማድረግ፥ አለምን መውደድ፥ከጌታ መራቅ፥ በንስሃ ከመመለስ ይልቅ በሃጢያት መቀጠልና የመሳሰሉት ናቸው።)
   ለ) መጭነቅና ማዘን የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? (ሃጢያትን መጥላታችንን ለጌታ የምናሳየው ሃጢያትን ስንሰራና የሃጢያትን ሃሳብ ስናስብ ስናዝን፥ቶሎ እስክንነጻ ድረስ ስንጨነቅ ነው)
   ሐ) በጌታ ፊት ራሳችንን ማዋረድ ለምን ያስፈልጋል? (ብዙ ጊዜ የምንጣላው ለክብራችን፥ ለሙብታችን፥ ለስማችን ብለን ነው። ግን እንደኢየሱስ ራሳችንን ካዋረድን ማንም ምንም ቢያደርግ አያዋርደንም። ስለዚህም ወደጥል አንሄድም።)

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት ዘጠኝ**
**በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር**
**የምንባብ ክፍል፡ 4፡11-17**
**የጥናቱ ዓላማ፡** በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ከሰዎች ጋር ወይም በኑሮአችን ሁሉ ነገሮች ባይመቹም ባይገቡንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግን እንድንኖር ለማስተማር።

***መግቢያ፡*** እግዚአብሔር ሁሉን እንድናውቅ አልሰጠንም። ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን ለምን እንደሚያደርጉ እውቀቱን አልሰጠንም። ዛሬ ወይም ነገ ምን እንደምንሆን ሙሉ እውቀት አልሰጠንም። እንድናውቅ የሰጠን ዛሬ ምን ማድረግ እንዳለብን ብቻ ነው። ልናደርገው የሚገባንን በጎ ስራ በቃሉ አስተምሮናል። ባወቅነውም አለመኖር ወይም ባላወቅነው ለመኖር መታገል ሁለቱም ሃጢአት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን በተገለጠልን እየታዘዝነው ባልተገለጠልን እየታመነው እንድንኖር ነው።

**ቁ.** 11-12 ፍርድን ለእርሱ መተው

4፡11 "ወንድሞች ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም" አብረውን ያሉ ወንድሞችና እህቶች ከጥፋት ወይም ከድካም ነፃ አይደሉም። ነገር ግን ያጠፉ ሲመስለን እኛ ስለነሱ ጥፋት ለማውራት መፍጠን የለብንም። አጠፉ ወይም አላጠፉም ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ነው። እሱ ነው የወንድሞች ፈራጅ። እኛ አይደለንም። ስለዚህ ተበዳዮች እኛ ብንሆንም ወይም ሌሎች፥ ፍርድን ለጌታ መስጠት አለብን። ሰዎቹ ያረጉትን ለምን እንዳደረጉ በእርግጥ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ፍርድ ቤት ሔደን ዳኛ እያለ የራሳችንን ፍርድ መስጠት እንደማንችል ሁሉ፥እውነተኛው እግዚአብሔር እያለ እኛ መፍረዳችን ሃጢያት ነው።

በዚህ ክፍል ማማት ማለት ስለሌላው ክፉ ነገር በሌላው ፊት ማውራት ነው። እውነተኛ ፍርድ ግን ከሳሽም ተካሳሽም ባሉበት የሚሆን ስለሆነ ማማት ትክክለኛና ፍትሃዊ ባህሪ አይደለም።

**ቁ.**13-15 በእርሱ ፈቃድ ማቀድ

ስለሌሎች ጥፋት ብቻ ሳይሆን በህይወታችን ነገ ምን እንደሚሆንም አናውቅም። ስለዚህ ለሚያውቀው ለእግዚአብሔር ራሳችንን አሳልፈን እየሰጠን መኖር አለብን።

በዚህ ክፍል የሚነግዱ ሰዎች ወይም ማንኛውም ሰራተኛ በእቅድ አይኑር ሳይሆን የሚለው በማቀድ ብቻ መኖር ስለማይቻል፥ ሁሉ ለሚቻለው፥ ነገን ለሚያውቀው ለሱ ፈቃድ መገዛት ይበጃል ይለናል።

ጌታ ከፈቀደ ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት አማራጭ ያለው እቅድ ይዘን እንኖራለን ማለት ነው። አማራጭ መያዝ በራሱ ችግር የለውም። በምዕራፍ አንድ ቁጥር 7ና8 ላይ ሁለት ሃሳብ ያለው የሚለው በእግዚአብሔር ታምኖ በመኖርና በገዛ መንገዱ በመሄድ የሚያወላውል ማለት ነው።

**ቁ.**16-17 የእርሱን ፈቃድ አውቆ ማድረግ

እግዚአብሔር ስለሌሎች ወይም ስለነገ እውቀት አልሰጠን ይሆናል ግን ስለበጎ ነገር እና ፈቃዱ ስለሆነው ነገር በቃሉ አሳውቆናል። ባወቅነው አለመኖር በማናውቀው ነገር እንደመኖር ሁሉ ሃጢያት ነው።

***መደምደምያ፡***
በዚህ ምድር ስንኖር በእውቀት የተወሰንን ነን። ስለ ሰዎችና ስለነገ ጥልቅ ነገር አናውቅም። ነገር ግን ዛሬ ማድረግ ያለብንን እግዚአብሔር ያሳውቀናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ባወቅነው እንድንታዘዘውና በማናውቀው እንድንታመነው ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1) 4፡11 ሰለማማት ይናገራል። ማማት ምንድን ነው? ማማት የተከለከልነው ለምንድን ነው?

ሀ) ማማት ከፍርድ ጋር እንዴት ይያያዛል? (ማማት አንድ ሰው ጥፋተኛ ነው ብሎ ለሌላ ሰው መንገር ስለሆነ፥ጥፋተኛ ነው ስንል ደግሞ ፈራጆች እየሆንን ነው ማለት ነው?)አዎን ከሆነ እንዴት?

ለ) ሕግን ማማት በሕግ መፍረድ ምንድን ነው? (የመፅሐፍ ቅዱስ ሕግ ሌላ ሰው ሲያጠፉ ጥፋቱን እንድንነግረው ወይም ለመሪዎቻችን እንድናቀርበው ወይም ለእግዚአብሔር እንድንሰጠው ስለሚናገር፥ ስናማ ከሕጉ ጋር የሚቃረን ነገር እያደረግን ስለሆነ ነው ማለት ነው? በሌላ አባባል ሕጉን ተሳስተሃል እያልኩ ነው ማለት ነው?)

2) 4፡11-12 ስለፍርድ ሲያወራ ሕግን የጠቀሰው ለምንድን ነው? ስለእግዚአብሔር ፈራጅ ሲናገረ ስለሕግ ሰጪነቱ የሚናገረው ለምንድን ነው? (እግዚአብሔር የሚፈርደው በሕግ ነው። እኛ በስሜት ነው የምፈርደው። እርሱ ግን በቃሉ ፍትህ ይሰጣል። በዚህ ትክክለኛ ሃሳብ ተወያዩ)

3) እግዚአብሔር ያድናልም ያጠፋልም የሚለው አባባል አይጋጭም? (ዳኛ አንዳንዱን ወደ ወይኒ ወይም ወደ ሞት እንደሚልክ አንዳንዱን ደግሞ ነፃ እንደሚለቅ ማለት ነው)በዚህ ሃሳብ ትክክለኛ አባባል ነው። እንዴት? ተወያዩ )

4)ቁጥር 13 ላይ ያሉ ሰዎች ንግግር ችግሩ ምንድን ነው? አማራጭ እቅድ መያዝ ችግር አለው? አገር መቀየር ችግር አለው? ስለዛሬ ወይም ስለነገ በእርግጠኝነት መናገር እንደማይችሉ እያወቁ በትዕቢት መናገራቸው ነው? እንዴት ነበር ማለት ያለባቸው?

5) ነገ የሚሆነውን መገመትና ማወቅ ልዩነቱ ምንድን ነው? አታውቁምም ወይም መገመትም አትችሉም ነው የሚላቸው?

6) በቁጥር 15 ላይ የሚያቅዱት ሰዎች ከቁጥር 13 ካሉት ጋር የሚለዩት በምንድን ነው?

7) አሁን ትመካላችሁ የሚለው ማንን ነው? በምንድን ነው የሚመኩት?

- የተወቀሱበት ምክንያት እስከዛሬ የሆነላቸው በጌታ እንጂ በእነርሱ ብርታት እንዳልሆነ መርሳታቸው ነው ማለት ነው? ለማብራሪያ ያህል ምዕራፍ አንድ የበጎ ምንጩ ጌታ እንደሆነ አትርሱ ይላል። እነዚህ ግን የረሱ ይመስላል።)

8) በቁጥር 17 ላይ ታውቃላችሁ የሚላቸው ምንድን ነው? ከዚህ በፊት አታውቁም ያላቸው ምንድን ነበር?

***መደምደምያ፡*** በዚህ ምድር ስንኖር በእውቀት የተወሰንን ነን። ስለሰዎችና ስለነገ ጥልቅ ነገር አናውቅም። ነገር ግን ዛሬ ማድረግ ያለብንን እግዚአብሔር ያሳውቀናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ባወቅነው እንድንታዘዘውና በማናውቀቅ እንድንታመነው ነው።

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት አስር**
**ትዕግስት**
**የምንባብ ክፍል፡ 5፡1-12**
**የጥናቱ ዓላማ፡** በመከራችን ሁሉ እስከሞት ወይም ጌታ እስኪመጣ ድረስ እንድንታገሥ ለማነሳሳት።

***መግቢያ፡*** ያዕቆብ መጀመሪያ ቅዱሳንን ለሚበድሉ ሰዎች ስለሚመጣባቸው ፍርድ ደግሞም አሁን እንኳ እየተቀበሉት ስላለው ፍርድ ይነግራቸዋል። ጌታ የተበዳዮችን ድምጽ እንደሚሰማ አውቀው አሁኑኑ በፍርሃት ሕይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ይነግራቸዋል። ወደ ተበዳዮች ዞር ብሎ ደግሞ ምንም አይነት መከራ ቢቀበሉም ጌታ ሊፈርድላቸው እንደሚመጣ አውቀው እንዲታገሱ ያዛቸዋል። እርስ በርስ በመካሰስ አንተ ነህ አንቺ ነሽ በመባባል ፈራጅ የሆነውን የጌታን ድርሻ እንዳይዙ፥ በመሃላም ከችግራቸው ለመውጣት እንዳይታገሉም ያስጠነቅቃቸዋል።

**ቁ. 1-6 ለበዳዮች የተሰጠ ፍርድ**
እግዚአብሔር የፍትህ አምላክ ስለሆነ ለተበዳዮች ይፈርዳል። ነገር ግን በዳዮች ከጥፋታቸው እንዲመለሱ እድል ይሰጣል። በዚህ ክፍል በደልን በሌላው ላይ ለሚያደርሱት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል አልቅሱ የሚላቸው የሚጠብቃቸውን ፍርድ አይተው በንስሃ እንዲመለሱ ነው። ከቁጥር 2 እስከ 3 በበዳዮች ላይ ስለደረሰው መርገም ነው የሚ.ጋናገረው። ዋናው ሃሳቡ ሃብታቸው እርካታ እንዳልሆናቸውና ምንም እንዳልጠቀማቸው ነው የሚናገረው። በዚህ ክፍል ባለጠጋ ማለት ተግቶ ሰርቶ ሃብታም የሆነን ሰው ሳይሆን በሌሎች ጉልበት፤በግፍ በቶሎ ሃብትን የሰበሰበን ነው።
ቁ 5 በሴሰኝነት መኖር ማለት ስጋችን የጠየቀንን ሁሉ ሃጢያት ቢሆንም ሌላውንም ቢጎዳ ማድረግ ነው።
ቁ 6 ጻድቅ ሰዎችን ባለጠጎችም ቢሆኑ ስለጥፋታቸው ይወቅሳል። ይህም አንዳንዴ ሞትን ሊያመጣ ይችላል። እናንተንም አይቃወምም የሚለው ከተገደለ በኋላ ስላለው እንጂ ጻድቅ አይቃወምም ማለት አይደለም።

**ቁ. 7-12 ለተበዳዮች የተሰጠ ምክር**
ከላይ ከቁጥር 1 እስከ 6 ድረስ ቅዱሳንን ለሚበድሉአቸው ማስጠንቀቅያን ከሰጠ በኋላ አሁን ደግሞ ከቁጥር 7 እስከ 12 ድረስ ለተበዳዮች ምክርን ይሰጣል። እግዚአብሔር የሚበድሉንን እንደሚያናግራቸውና በጊዜ ደግሞ ወደፍርድ እንደሚያመጣቸው ካወቅን ለመታገሥ ይረዳናል።
**ቁ.** 7-8 ጌታን ጠብቁ
ቅዱሳን መታገሥ ያለባቸው ጌታ እስኪመጣ ድረስ ነው። የፊተኛውና የኋለኛው ዝናብ የሚያመለክተው በዚህም ዘመን በሚመጣውም ከጌታ የምንቀበለውን በረከት ነው። አንዳንዴ እዚህ ምድር ላይ አንዳንዴ ደግሞ ከሞት በኋላ ከጌታ ብድራትን እንቀበላለን። ትዕግሥት ያለው ሰው ልቡን ያጸና ነው። የልብ ጽናት የሚያስፈልገው በመከራ ውስጥ እንዳናወላውል ነው።

ቁ 9 ፈራጅ እግዚአብሔር ነውና እርስ በርሳችን አንተነህ ጥፋተኛ መባባል የለብንም። ማጉረምረም ማለት አንተ ነህ አንቺ ነሽ ጥፋተኛ መባባል ነው።

ቁ 10-11 ከቅዱሳን አባቶች ተማሩ
በትዕግሥት መጽናት ማለት በመከራ ውስጥ ሳለን እምነታችንን፥ ንጽህናችንን ሳንጥልና፥ ሌላውም ላይ ሳንፈርድ፥ ጌታን ሳንክድ ጠብቀን መከራውን ማሸነፍ ሲርቅ ማለት ነው። ጌታም እንደፈጸመለት ማለት ጌታ ዓላማውን በኢዮብ እንደፈጸመው ማለት ነው። እግዚአብሔር ከሰይጣን ጋር ሊወራረድ ነው ኢዮብ መከራን የተቀበለው። እግዚአብሔር ሃሳቡ ተፈጽሞአል።

12 ወደመከራ እንዳንገባ ወይም ከመከራ ለመውጣት ስንል ብዙ ዓይነት ቃል ኪዳን ልንገባ እንችላለን። ለምሳሌ መሳፍንት 11 ቁ 30 ጀምሮ እንደምናየው ዮፍታሔ ቸኩሎ በእግዚአብሔር ፊት ማሃላ(ስለት) አቀረበ። እግዚአብሔር ያለሱ ማሃላ ይረዳው ነበር። ማሃላ ከማቀረብ ጌታን በትዕግሥት መጠበቅ ይሻላል።

***መደምደምያ፡*** እግዚአብሔር የሚበድሉንን እኛን ወክሎ እንደሚያናግርልንና በጊዜው ደግሞ እንድሚፈርድልን አውቀን፤ጌታ እስኪመጣ ድረስ ማንኛውንም መከራ እንድቅዱሳ አባቶቻችን ልባችንን አጽንተን ልንታገሥ ይገባል።
***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

1)5፡1-6 የሚደርስባቹ ጭንቅ የሚለው ምኑን ነው? ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ የሚላቸውን ለምንድን ነው? ጭንቅ የሚለው ወደታች ለተዘረዘረው ሃጢያታቸው ከሞት በኋላ የሚፈረድባቸውን ፍርድ ነው ብለን ማሰብ እንችላለን? አልቅሱ የሚላቸውስ ንስሃ እንዲገቡ ማለት ነው?

2) ከቁጥር 2-3 የባላጠጎች ሃብት ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነው ያለው? ሃብታቸው ምን ሆኖአል ነው የሚላቸው?

3) የነዚህ ሰዎች ችግሩ ሃብታም መሆን ነው ወይስ ሃብታቸውን የሰበሰቡበትና የያዙት መንገድ ነው?

4) ከቁጥር 4-6 ድረስ የተዘረዘረው የእነዚህ ሰዎች ሃጢያት ምን ምንድን ነው?

5) ቁጥር 6 ላይ "እናንተን አይቃወምም" ሲል ለምንድን ነው ጻድቅ ባለጠጎችን የማይቃወመው? በርግጥ ሰው ከሞተ በኋላ ለቃወም አይችልም። እንደዚህ ማለት ነው?

6) ጌታ እስኪመጣ ታገሡ ሲል ማንን ወይም ምንን ነው መታገሥ የሚያስፈልገው?ከቁጥር 1 እስከ 6 ያለው ለቅዱሳን ትዕግሥት ምን ይረዳል?

7) ትዕግሥት ምንድን ነው? በቁጥር 8 ላይ የታገሠ ሰው ምን ይመስላል?

8) ስለጌታ መምጫ ቅርበት የሚነግራቸው ለምንድን ነው? ይህ ሃሳብ ከፍርድ ጋር ግንኙነት አለው?

9) እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ ሲል ምን ማለቱ ነው? አትካሰሱ፥ አንተነ አንቺ ነሽ ጥፋተኛ አትባባሉ ማለቱ ነው? ለምን አታጉረምርሙ ይላል?

10) በትዕግሥት የጸኑት እነ ኢዮብ የተቀበሉት መከራና በዚህ ክፍል በባለጠጎች እጅ እየተሰቃዩ ያሉት ሰዎች መከራ ይነጻጸራል?ኢዮብ ከሰዎችም መከራ ተቀብሎአል ማለት ነው? ከነኢዮብ ምን እንማራለን?

11) አትማሉ የተባለው ለምንድን ነው? ማሃላ ከትዕግሥት ጋር ምን አገናኘው? ተጨማሪ ማብራሪያ፡-ምን አልባት ከሚቀበሉት መከራ ለመውጣት ወይም ወደ መከራው ከመጀመርያ ላለመገባት ብለው የማሉት ይሆናል። ይህ ከሆነ ደግሞ ከመከራ የሚያወጣ ወይም እንዳንገባ የሚጠብቀን እርሱ እንደሆነ አምነን ከመሃላ እንድንጠበቅ ብሎ ነው።

**የያዕቆብ መልዕክት - ጥናት አስራ አንድ**
***ፀሎት***
**የምንባብ ክፍል፡ 5፡13-20**
**የጥናቱ ዓላማ፡-** ፀሎትን በግል፥ከሌሎች ቅዱሳን ጋር እና ከአገልጋዮች ጋር እንድንለማመድ ለማነሳሳት

***መግቢያ፡-*** የግል ፀሎት ሁላችንም ሊኖረን ይገባል። አንዳንዴ ግን መፀለይ ሊያቅተን ይችላል። የፀሎት አቅም ስናጣ በሌሎች ፀሎት መደገፍ እንዳለብን ያዕቆብ ያስተምራል። አንደኛ በአገልጋዮች ፀሎት መደገፍ ይገባናል። ሌላው ደግሞ አገልጋይ ብቻ መጠበቅ የለብንም። አብረውን ያሉ ቅዱሳን በፀሎት ሊደግፉን ይችላሉ። ስለዚህ ለአገልጋዮችም ለሌሎች ቅዱሳንም የፀሎት ጥያቄአችንን እያቀረብን በፀሎታቸው ልንደገፍና አቅማችንን ልናድስ እንችላለን።

***ቁ.*** 13 ይህ ክፍል ስለግል ፀሎት የሚያስተምር ነው። ያዕቆብ መናገር የሚፈልገው አንድ አማኝ ብቻውንም መፀለይ እንዳለበት እንጂ መቼ መፀለይ እንዳለበት አይደለም። ስለዚህ መከራ ሲኖርባችሁ ብቻ እንጂ ደስ ሲላችሁ አትፀልዩ አለለም። አማኝ ሁል ጊዜ መፀለይ አለበት ግን በዚህ ክፍል መሰረት አንዳንዴ ብቻውን አንዳንዴ ደግሞ ከሌሎች ጋር መፀለይ እንዳለበት እንማራለን። በዚህ ክፍል መከራ ሲል ማንኛውንም ዓይነት መከራ ማለት ነው። መከራ ሲመጣ ከማጉረምረም ወይም በገዛ መንገዳችን ከመሄድ ይልቅ በፀሎት መከራን መጋፈጥ እንዳለብን እንማራለን። ሌላው መከራ የሚቀበል አይዘምር ማለቱ ሳይሆን፥ ማንም ሰው ካልፀለየ መደሰት እንደማይችልና ሳይደሰቱ ደግሞ መዘመር እንደሚያስቸግር ለማሳየት ነው። ለምሳሌ ሐዋ 16፡5 ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት መከራ ሲቀበሉ ይፀልዩና በዜማ ያመሰግኑ ነበር። ፀሎት ወደ ምስጋና ይመራል።

***ቁ.*** 14-15 አንዳንዴ በግላችን መጸለይ ሊያቅተን ይችላል። ሲደክመን ጌታ አይፈርድብንም። ነገር ግን በጸሎት የሚሸከሙንን አገልጋዮች ሰጥቶናል። የአገልጋዮችን ጸሎት ሲያመን ብቻ እንድንፈልግ ሳይሆን የሚናገረን እንደ አንድ ምሳሌ ነው የሚያቀርበው። ጸሎት የሚያቅተን አንዱ ሲያመን ነው። ዘይት ካልቀቡ መጸለይ አይቻልም ወይም ሃይል ያለው ዘይቱ ላይ ነው እያለ ሳይሆን እምነታቸውን እንዲረዳ ዘይት ይጠቀሙ ማለቱ ነው። የሚያድን ጌታ ነው። ጌታ ደግሞ የሚያድነው አምነው ሲጠይቁት ነው። ኃጢአት ሰርቶ ከሆነ ሲል የበሽታ ምንጩ ሁልጊዜ ኃጢአት እንዳልሆነ ያሳያል። ንስሃ ሳይገባ ኃጢአት ይሰረያል ማለት ሳይሆን የታመመው ሰው ማናገር ባይችል እንኳ ጸሎት እስከ ፈለገ ድረስ ጌታ የስጋም የነፍስም መዳን ይሰጣል ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ መናገር ያልቻለውን አካል ጉዳተኛ ፈውሶ ኃጢያትህ ተሰረየችልህ ብሎታል። ጌታ ሁሉንም ይችላል።

***ቁ.*** 16-20 ፀሎትን በግልና ከአገልጋዮች ጋር ብቻ ሳይሆን አብረውን ካሉ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ልንጸልይ እንደምገባን ያሰምረናል። አብረን ስንጸልይ ግን ማወቅ ያለብን ነገሮች አሉ። አንደኛ የራሳችንን ሃጢአት መናዘዝ አለብን። ችግራችንን ደብቀን ጸልዩልኝ ማለት አያዋጣም። ትፈወሱም ዘንድ ሲል የስጋም የነፍስም ፈውስ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛ የሌሎችን ሃጢአት ማውራት ሳይሆን ከሃጢአታቸው መመለስ አለብን (ቁ 19-20)።

ለሌሎች ስንጸልይም ወይም የሚጸልዩልን ሰዎች በእምነት መጸለይ አለባቸው። እግዚአብሔር ከአፋችን የሚወጣውን ቃል ሳይሆን እምነታችንን ነው የሚያየው።

17-18 ኤልያስ የፀሎት ምሳሌ ነው። እንደኛ ሰው ነው። አጥብቆ ወይም ደጋግሞ መልስ እሲክቀበል ድረስ ጸለየ። አምኖ ጸለየ። የጸሎትን መልስ ተቀበለ።

***መደምደምያ፡*** ሁል ጊዜ በጸሎት መትጋት አለብን። ግን ሁል ጊዜ ብቻችንን መትጋት አንችልም። አንዳንዴ ልንደክም እንችላለን። እግዚአብሔር ብዙ አገልጋዮችንና ቅዱሳንን በዙሪያችን ስለሰጠን እርስ በርስ ተደጋግፈን ሁልጊዜ በጸሎት መትጋት አለብን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡*** **(በሁለት ቀን መወያየት ትችላላችሁ)**

1) 5፡13 ላይ መከራ የሚቀበል ሲል ምን ዓይነት መከራ ነው የሚለው?

1.1 መከራ የሚቀበል ሰው ከመዘመር ይልቅ ፀልይ የተባለው ለምንድን ነው?

ጸሎት ለምስጋና መንገድ ይከፍታል ማለት ነው?

1.2 ደስ ያለው መዘመር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

1.3 ደስ ያለው መፀለይ አያስፈልገውም? አንዳንድ ጊዜ ከመፀለይ ይልቅ አመስግን የሚሉ ሰዎች ሲያጋጥሙ በዚህ ክፍል መሰረት ምን ልንላቸው ይገባል?

2)5፡14-15 ከእናንተ መካከል የታመመ ቢኖር ሲል አማኝ ሊታመም ይችላል ማለት ነው?

2፤1 ሲታመም እራሱ ከመጸለይ ይልቅ አገልጋዮችን ይጥራ ያለው ለምንድን ነው? ከህመማችን የተነሳ በእምነታችን ልንደክም ልንጠራጠር እንችል ይሆናል ማለት ነው? እንደዚህ ማለቱ መንፈሳዊ ኑሮ እርስ በርስ መደጋገፍ ያለብን ኑሮ እንደሆን ሊያመለክተን ነው ብላችሁ ትስማማላችሁ?

2፤2 ሽማግሌዎች ማለት በኛ ዘመን የሽምግልና አገልግሎት የሚያገለግሉትን ብቻ ማለቱ ነው ወይስ ሁሉንም አገልጋዮችን ያጠቃልላል?

2፡3 ዘይት ቀብተው መጸለያቸው ጥቅሙ ምንድን ነው? ያለ ዘይት መጸለይ አይቻልም?

2፡4 ድውዩን ወይም በሽተኛውን የሚያድነው ምንድን ነው? ይህስ ምንን ያስተምራል?

2፡5 ኃጢአት ሠርቶ እንደሆነ ሲል በሽታ ከኃጢያትም ሊመጣ ይችላል ማለት ነው?

2፡6 ኃጢያት ንስሃ ሳይገባ ይሰረያ እያለ ነው? (ማስታወሻ፡- መናገር ያቃተው በሽተኛ ከሆነ ንስሃ መናገር አይችልም ማለት ነው። ነገር ግን ጸሎትን መፈለጉ እንደንስሃ ይታይለታል።)

**<u>ለሁላተኛ ቀን</u>**

3) እርስ በርስ ስንጸልይ ልናደርግ የሚገባን ነገር ከ ቁ 16 እስከ 20 ምን ምንድን ነው?

3፡1 ሃጢያት መናዘዝ ያለብን ለምንድን ነው? ሃጢያታችንን ሳንናገር መጸለይ አይቻልም?

(እውነተኛ ፈውስ እንዲመጣ መናዘዝ አለብን። እግዚአብሔር እራሱ ለሌላው ሰው እስኪገልጥ መጠበቅ የለብንም።)በዚህ ሀሳብ ተወያዩ። ምስጥር መጠበቅ አለበት።

3፡2 እንደ ኤልያስ መጸለይ የሚችለው ማነው? አገልጋይ ብቻ ወይስ ማንም አማኝ?

(ማስተወሻ፡-ስለ አገልጋዮች ሳይሆን ስለእርስ በርስ ሲያወራ ነው ኤልያስን የጠቀሰው ስለዚህ ማናችንም እንደኤልያስ መጸለይ እንችላለን)

3፡3 ከኤልያስ የምንማረው ምንድን ነው?

3፡4 አብረውን የሚጸልዩ ሰዎች ወይም ሌሎች ሃጢአት ሲሰሩ ምን ማድረግ አለብን?

3፡5 ሃጢያት አንዳንዴ በሽታን ግን ደግሞ በቁ 20 መሰርት ምን ሊያመጣ ይችላል?

ጌታ ጸሎታችሁን በመስማት ይባርካችሁ!ይህ ጥናት ለሕይወታችሁ የሚጠቅም ይሁን።

በአሥራ አንዱም ጥናት ማንኛውም ዓይነት አስተያየት ወይንም ጥያቄ ካልዎት በሚቀጥሉት ገጾች ያስቀምጡ (ይጻፉ)። አስተያየትዎንም በመሪዎቻችሁ በኩል ቀጥታ ለትምህርት ክፍሉ ያሳውቁ። ጌታ ይባርክዎት!
ጥናትአንድ

**ጥናት ሁለት**

**ጥናት ሶስት**

**ጥናት አራት**

**ጥናት አምስት**

**ጥናት ስድስት**

**ጥናት ሰባት**

**ጥናት ስምንት**

ጥናት ዘጠኝ

ጥናት አስር

ጥናት አስራ አንድ

አጠቃላይ አስተያየት